# የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን

# Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority

# የመኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የምዝገባና የሥራ ፈቃድ ማስጫአሠራር መመሪያ 12/2012

| አንቀጽ | ማውጫ | ገጽ |
|---|---|---|


መግቢያ....................................................1
1. አጭር ርዕስ....................................................5
2. ትርጓሜ....................................................5
3. የመመሪያዉ ዓላማ....................................................7
4. የተፈጻሚነት ወሰን....................................................8
5. የመኖ ንግድ....................................................8
6. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ መስጠት....................................................8
7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መሠረታዊ መስፈርቶች....................................................9
1. የመኖ አምራች ወይም ላኪ ድርጅት ማሟላት የሚገባዉ መስፈርቶች....................................................9
2. የመኖ አስመጪ ድርጅት ማሟላት የሚገባዉ መስፈርቶች....................................................10
3. የመኖ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ማሟላት የሚገባዉ መስፈርቶች....................................................11
4. የመኖንግድ ሥራ ባለሙያ ማሟላት የሚገባው መስፈርቶች....................................................12
5. በመኖ ንግድ የማማከር ሥራ ባለሙያ ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች....................................................13
8.የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማይጠየቅባቸዉ ልዩ ሁኔታዎች....................................................14
9.የንግድ አድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ....................................................14
10. ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ስለመስጠት....................................................12
11. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት....................................................15
12. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ....................................................15
13. የመኖ ንግድ ድርጅት ስለሚቋቋምበት አካባቢ ሁኔታዎች....................................................16
14. የመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ ግንባታ አሠራር....................................................16
15. በመኖ ማከማቻ መጋዘን ዉስጥ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች....................................................17
16. የመኖ እና መኖ ግብዓት መያዣ ወይም ማሸጊያ ዕቃዎች ሁኔታ....................................................18
17. በመኖ እና መኖ ጥሬ ዕቃወይም ግብዓት መያዣ ላይ መኖር ስለሚገባዉ ገላጭ ጽሑፍ....................................................18
18. ስለ መኖ የቴክኒክ ሠራተኛ የሙያ ብቃት ደረጃዎች....................................................19
19. የመኖ ንግድ ድርጅት የቴክኒክ ሠራተኛ እና ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት....................................................20
20. መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ-ነገሮችንወይም ግብዓቶችን ወደ ሀገርውስጥ ስለማስገባት....................................................20
21. በመኖወይምየመኖ ንጥረ-ነገሮችጤናሰርተፊኬትላይመካተትያለባቸውመረጃዎች....................................................21
22. በመኖ ወይም የመኖ ግብዓቶች ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት ላይ መካተት ያለባቸው መረጃዎች....................................................22
23. መኖ እና የመኖ ንጥረ-ነገርወይም ግብዓት ከሀገር ስለማስወጣት....................................................22
24. የመኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይም ግብዓቶች አከመቻቸትና አያያዝ ሁኔታ....................................................23
25. መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገርወይም ግብዓቶችን ስለ ማከፋፈል....................................................24
26. መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችንወይም ግብዓቶችን ስለማጓጓዝ....................................................24
27. ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት....................................................25

28. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕገዳ........25
29. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ........26
30. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለባለሥልጣኑ ስለመመለስ........26
31. የብቃት ማረጋገጫ ዕገዳ ስለማንሳትና የተሰረዘውን ስለመተካት........27
32. የመኖ ምርቶችንና ግብዓቶችን ለሌላ አካል ስለማስተላለፍ........27
33. መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችን ስለመያዝ........27
34. የመኖ ምርት ከገበያ ስለመሰብሰብ (Feed Products Recall)........27
35. ጥቅም ላይ የማይውሉ የመኖ ምርቶችንና ንጥረ-ነገሮችንወይም ግብዓቶችን ስለማስወገድ........28
36. በሚወሰዱ አስተዳዳራዊ እርምጃዎች ላይ የቅሬታ አቀራረብ ሂደት........28
37. የመኖ መረጃ ስለ መያዝ........29
38. የመኖ ምርት ወይም ግብዓት የንግድ ማስታወቂያ አሠራር........29
39. የመኖ መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለ ማድረግ........31
40. የአገልግሎት ክፍያ........31
41. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች........32
42. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ........32
43. ዕዝሎች........31

## መግቢያ

በእንስሳት መኖ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩና የሚሰማሩ ድርጅቶች የሚያመርቱትን፣ ከዉጭ ወደ ሀገር የሚያስገቡትን፣ ሚያከፋፍሉትን ወይም ከሀገር ወደ ዉጭ የሚልኩትን የመኖጥራትና ደህንነት  በማረጋገጥ የቀጥተኛ ተመጋቢዉን እንስሳ እንዲሁም የእንስሳት ምርት ተጠቃሚዉን ህብረተሰብ ጤና መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ወደ ሀገር የሚገባ መኖ እና መኖ ግብዓት ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠና አስፈላጊ መስፈርቶችን ያሟላ  መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በእንስሳት መኖ ላይ በቂና ሕጋዊ ቁጥጥር ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመኖ ንግድ ሥራ ላይ ለሚሰማራ  ማንኛውም ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ መከታተልና  መቆጣጠር አስፈላጊ የንግድ አሠራር ሥርዓት ሆኖ በመገኘቱ፤

የመኖ ንግድ ሥራ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ሥራዎችን ግልጽና ተጠያቂነት በሰፈነበት አሠራር ለማካሄድ እንዲቻልና ተገልጋዮችም ይህንን አውቀው መደረግ የሚገባውን ቅድመ ዝግጅት በማሟላት የአገልግሎት ጥያቄአቸውን በአግባቡ እንዲያቀርቡ ለማስቻል፤

በኢትዮጵያ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳዳርና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 ለእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነትመሠረትይህ የመኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የምዝገባና ፈቃድ መስጫ አሠራር መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህመመሪያ "የመኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይና ላኪ ድርጅቶች የምዝገባና የሥራ ፈቃድ መስጫ አሠራር መመሪያ ቁጥር 12/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 2. ትርጓሜ

በአዋጁ አንቀፅ 2 ሥር ለተመለከቱ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡-

1. "መኖ" ማለት በመኖ አምራችድርጅት ተመርቶ፣ተገዝቶ ወይም ተቀነባብሮ በሀገር ዉስጥ የሚመረት፣ ከዉጭ ወደ ሀገር የሚገባ፣ በሀገር ዉስጥም ከአንድክልል ወደ ሌላ ክልል ለንግድ የሚዘዋወር ወይም ወደ ውጭ ሀገር ገበያ ለሽያጭ የሚወጣ የእንስሳት ምግብ ነው፡፡ ይህ ትርጉም ወደ ንግድ ቅብብሎሽ የሚገባዉን የሣር ድርቆሽ፣የአገዳና ብርዕ ሰብሎች ተረፈ ምርትንና የጤፍ ጭድን የሚያካትት ሲሆን የንግድ መኖ መዘርዝር በሌላ ሰነድ የሚዘጋጅ ይሆናል፤
2. "የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር" ማለት ማንኛውም መደበኛ የእንስሳት አመጋገብን የንጥረ መኖ ፍላጎት ለማሟላት በይዘቱ የምግብነት ወይም መኖነት ያለዉ ወይምየሌለዉ ሆኖ በመኖ ዝግጅት ወቅት ለማጣፈጫ፣ ለቀለም ማሳመሪያ ወይም ለማጣበቂያ (ቅርጽ ማስያዣ) ወዘተ በጥቂቱ የሚቀላቀል ንጥረ ነገር ሆኖ በእንስሳት ወይም በእንስሳት ምርት ተመጋቢ ክፍል ላይ ምንም ዓይነት የጎንዮሽ ጉዳት እንደማያስከትል የተረጋገጠ መጠነኛ ንጥረ ነገር ነዉ ፤
3. "የመኖ ግብዓት" ማለት ተፈላጊውን መሠረታዊ መኖ ለማዘጋጀት የሚያገለግል መደባለቂያ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም ተጨማሪ ንጥረ-ነገር ነው፤
4. "ዘረመሉ የተለወጠ ወይም ልውጥ ሕያው የመኖ ግብዓት" ማለት በዘመኑ የዕፀዋትና እንስሳት ርቢ ምህንድስና፣ በሰው ሠራሽ ዘዴ ከሌላ ሕያው የተወሰደ ወይም እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረመል ወይም ሌላ ንጥረ ነገር የተጨመረበት የዘረመሎች ይዘት፣ አቀማመጥና ባህርይ የተለወጠበትሕያው የእንስሳትና የዕፅዋት ውጤት ነዉ፤
5. "ከአመንዣኪ እንስሳት ምርት የተገኘ የመኖ ግብዓት" ማለት የሚያመሰኩ እንስሳት (የዳልጋ ከብት፣ ጎሽ፣ በግ፣ፍየል፣ግመል እና የመሳሰሉት) የተፈጨ ሥጋ፣ የደም፣ የአጥንት፣ የአንጎል፣ የአንጀት እና ሌሎች ምርት ዉጤት ነዉ፤
6. "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለትበመኖ ንግድሥራላይ ለሚሰማራ ማንኛዉምድርጅት ወይም ተቋም አስፈላጊ ተቋማዊና የሰው ኃይል መስፈርቶችን አሟልቶ

ሲገኝ የንግድ ሥራውን ለማካሄድ የሚያስችል በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የብቁነት ማረጋገጫ ወይም የሥራ ፈቃድ ነዉ፤

7. “የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት ለእንስሳት መኖ ባለሙያ በመኖ ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት የሚያስችል በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነዉ፤

8. “የእንስሳት መኖ ባለሙያ” ማለት ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ወይም ተቋም በእንስሳት ሳይንስ ወይም በእንስሳት መኖ እና ግጦሽ ልማትና አስተዳደር በዲፕሎማ ወይም በመጀመሪያ ዲግሪ እና በላይ የተመረቀ/ች እንዲሁም በመኖና በእንስሳት ሥነ-ምግብ ተጨማሪ ሥልጠና የወሰደ/ች ነዉ፤

9. “የመኖ ፈቃድ ሰጪ አካል” ማለት በባለሥልጣኑ የመኖ ጥራት ደረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ወይም ዉክልና የተሰጠዉና ለተግባሩም አግባብነት ያለዉ አካል ነዉ፤

10. “የመኖ ንግድ” ማለት የእንስሳት መኖን ለንግድ ተግባር ማምረት፣ማዘጋጀት፣ ከዉጭ ሀገር ማስገባት፣ ወደ ዉጭ ሀገር መላክ፣ ክልል ተሻጋሪ የጅምላ ማከፋፈል ሥራ ነዉ፤

11. “የመኖ ንግድ ድርጅት” ማለት ለንግድ ዓላማ መኖን የሚገዛ፣ የሚያመርት፣ ከዉጭ የሚያስመጣ፣ ወደ ዉጭ ሀገር የሚልክ ወይም በሀገር ዉስጥ በጅምላ በማከፋፈል ሥራ ላይ የተሰማራ ተቋም ነው፤

12. “የመኖ ላኪ” ማለት በሀገር ዉስጥ የተመረቱትን የእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችን በየብስ፣ በባሕር ወይም በአየር ከኢትዮጵያ ወደ ዉጭ ሀገር የሚልክ ሰው ወይም ድርጅት ነዉ፤

13. “የመኖ አስመጪ” ማለት ከሀገር ዉጭ የተመረቱ የእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችንበአየር፣ በየብስ፣በባህር ወደ ሀገር በማስገባት ለመኖ ወይም ለመኖ ግብዓት ጅምላ አከፋፋዮችናቸርቻሪዎች የሚያከፋፍል ተቋም ወይም ድርጅት ነዉ፤

14. “የመኖ ጅምላ አከፋፋይ” ማለት ከሀገር ዉስጥ መኖ አምራች ወይም አስመጪ በጅምላ በመግዛት ለመኖ ቸርቻሪዎች የሚያከፋፍል ተቋም ወይም ድርጅት ነዉ፤

15. “የእንስሳት መኖ መሸጫ” ማለት የእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችና ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች የሚሸጡበት መደብር ወይም ድርጅት ወይም ተቋም ነዉ፤

16. “የመኖ ደረጃዎች” ማለት በሀገሪቱ የደረጃዎች ኤጀንሲ የፀደቀና ኦፊሴላዊ ተቀባይነት ያገኘ የመኖ ጥራትና ደህንነት እንዲሁም ጤናማነቱ የተረጋገጠ መኖ ነዉ፤

17. “የመኖ ማሸጊያ ወይም መያዣ” ማለት የእንስሳት መኖ እንዲሁም የመኖ ግብዓቶችን ለመያዝ፣ ለማጓጓዝና ለማከማቸት የሚጠቀሙበት መያዣ ዕቃ ነዉ፤

18. “የመኖ ገላጭ ጽሑፍ” ማለት በመኖ መያዣ ዕቃ ላይ የሚጻፍ ወይም የሚለጠፍ ወይም የሚታሰር ሆኖስለ መኖዉ ዓይነት፣ የንጥረ ነገር ይዘት፣ ለምን ዓይነት እንስሳት አመጋገብ

እንደሚዉል፣ የተመረተበት ቀን፣ የአጠቃቀም አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን፣ የአያያዝና ክምችት ሁኔታ ወዘተ የሚገልጽ ነዉ፤

19. “መኖን አስመስሎ ማቅረብ” ማለት የመኖ ይዘታቸዉ ከተቀመጠዉ ደረጃ በታች ወይም በይዘት ሳይሆን በዕይታ ብቻ ተመሳሳይ ወይም በሚያስመስሉ ባዕድ ነገሮች መኖን አስመስሎ ማቅረብ ነዉ፤

20. “መኖን መከለስ” ማለት ጥራትና ደህንነቱ አስተማማኝ ከሆነ ታዋቂ የመኖምርት ጋር ዝቅተኛና ተፈላጊውን ደረጃ በማያሟላ ወይም ባዕድ ነገር ጋር በመቀላቀልና በመከለስ ለገበያ ማቅረብ ነዉ፤

21. “የመኖ ጤና ምስክር ወረቀት” አንድ የመኖ ምርት ጤናማ ስለመሆኑና መኖዉን ለሚመገበዉ እንስሳ ወይም የእንስሳዉን ምርት ዉጤት (ሥጋ፣ ወተት፣ ዕንቁላል ወዘተ) በሚመገበዉ አካል ላይ የጎንዮሽ የጤና ጉዳት እንደማያስከትል የሚያረጋግጥ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ነዉ፤

22. “የመኖ ንግድ ሥራ ፈቃድ ዕገዳ” ማለት በመኖ ንግድሥራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ወይም ተቋም ባለሥልጣኑ ያወጣቸውንና ተለይተው የተቀመጡ መስፈርቶችን ባለማክበሩ ምክንያት በዚህ መመሪያ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ ከመኖ ንግድ ሥራ ታግዶ እንዲቆይ የሚያደርግ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤

23. “የመኖ ንግድ ሥራ ፈቃድ መሰረዝ” ማለት በመኖንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ወይም ተቋም ባለስልጣኑ ያወጣቸዉንናተለይተው የተቀመጡ መስፈርቶችን ባለማክበሩ ምክንያት በመኖ ንግድ ሥራ ላይ እንዳይሰማራ ለማድረግ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በመሰረዝ የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ነው፤

24. “የመኖ ጥራት ምርመራ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት” ማለት እንደቅደም ተከተሉ በሀገር ውስጥ ለሚመረት፣ ወደ ሀገርለሚገባ ወይም ከአገር ለሚወጣ የመኖ ይዘትን የሚገልጽና ደህንነትን የሚያረጋግጥ ሥልጣን በተሰጠዉ ተቆጣጣሪ የውጪ ሀገር አካል ወይም በባለሥልጣኑ የሚሰጥ ሰነድ ነው፤

25. “ባለሥልጣን” ማለት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው

26. “አዋጅ”ማለት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አሰተደደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 ነው፤

27. ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ወይም ተቋም ማለት ነው፡፡

## 3. የመመሪያዉ ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ የመኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ላኪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ተቋማዊ

ብቃታቸዉን በማረጋገጥና አግባብነት ያለዉን የሥራ ፈቃድ በመስጠት የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነትን አስተማማኝነት በመጠበቅ ጤናማ የእንስሳት ምርት ዉጤት ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ለማስቻል ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገሪቱክልል እና ድንበር ተሻጋሪ የሆነ መኖ ማምረት፣ ማስመጣት፣ ጅምላ ማከፋፈል፣ ወደ ዉጭ መላክ እንዲሁም በመኖ ባለሙያነት ንግድ ሥራ ላይ በተሰማሩና በሚሰማሩ ሁሉ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት
# የመኖ ንግድ እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

## 5. የመኖ ንግድ

1. ማንኛዉም ሰው ከባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑን ከሚወክል አካል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያገኝ በእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ/ግብዓት ንግድሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፤
2. ማንኛዉም ሰው በመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ/ግብዓት ንግድ ሥራ ለመሰማራት የሚያስችል አስፈላጊ የብቃት ማረጋጋጫ ለማግኘት ከአንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 1 እስከ ንኡስ አንቀጽ ድረስበዝርዝር የተመለከቱትን መሠረታዊ መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ሰው በአዋጅ ቁጥር 686/2002 መሠረት የንግድ ሚ/ር ወይም ሚንስቴሩን ከሚወክል አካል የንግድ ፈቃድ ሳያገኝ በእንስሳት መኖ ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

## 6. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትስለመስጠት

1. ማንኛውም ሰው የመኖ ንግድ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ስር የተጠቀሱትን መስፈርቶች በማሟላትና በዕዝል አንድሥር የተመለከተዉን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት፤
2. የጠያቂዉ ድርጅት ወይም ተቋም ቅድመ ዝግጅትና ማመልከቻ የተሟላ ሲሆን ባለሥልጣኑ ከመኖ ጥራት ደረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት የተዉጣጣ ከሁለት አባላት ያላነሰ የአጣሪ ቡድን በመላክ ጠያቂዉ አካል ተገቢዉን ክፍያ ሲያሟላ ድርጅቱ እንዲታይለት ይደረጋል፤
3. የመኖ ወይም የመኖ ግብዓት ንግድ ድርጅቱአስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላቱ በባለሥልጣኑ ሠራተኞች በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች መሟላታቸዉን በመፈተሽና

በማረጋገጥ የብቃት ምስክር እንዲሰጠዉ ይደረጋል፤

4. ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ አስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላቱ በባለሥልጣኑ ከተረጋገጠ እና ተገቢዉን የአገልግሎት ክፍያ ከከፈለ በኋላ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫዉን በሦስት የሥራ ቀናት ዉስጥ አጠናቅቆ ይሠጣል፤
5. በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 1 እስከ ንኡስ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን መሠረታዊ መስፈርቶች እንደ አግባብነታቸዉ በበቂ ሁኔታ ሳይሟሉ ለጠያቂዉ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አይሰጥም፣የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የማይሰጥበት ምክንያቶችም በዝርዝር በጽሑፍ እንዲደርሰዉ ይደረጋል፡፡ በዚሁ መሠረት ድርጅቱ እንዲያሟላ በጽሑፍ የተሰጠዉን መስፈርት አስተካክሎ ስለመገኘቱ ሲረጋገጥ ተገቢዉን ክፍያ በማስከፈል እንደገና ታይቶና ተረጋግጦ በተቀመጠዉ መስፈርት መሠረት የምስክር ወረቀቱ ሊሰጠዉ ይችላል፡፡

## 7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያበቁ መሠረታዊ መስፈርቶች

### 1. የመኖ አምራች ወይም ላኪ ድርጅት ማሟላት የሚገባዉ መስፈርቶች

1. ማንኛዉም ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡

ሀ. ከነባር የመኖ ማምረቻ ተቋማት በስተቀር ማንኛውም የመኖ ማምረቻ ድርጅት ከሕዝብ መኖሪያ፣ ከጤና እና ማህበራዊ አገልግሎት መስጫድርጅት እንዲሁም ከእንስሳት ዕርባታ ጣቢያዎች ከ300 - 500 ሜትር ባላነሰ ርቀት ወይም ለኢንዱስተሪ ዞን በተከለለ አካባቢ መገኘት ይገባዋል፡፡

ለ. የመኖ ጥሬ ዕቃ መፈተሻና መረከቢያ ክፍል፣ የጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን፣ የማምረቻ ሰንሰለት፣ የምርት ጥራት ፍተሻና ቁጥጥር ክፍል፣ የምርት መጫኛና ማራገፊያመደላድል፣ ያለቀለት ምርት ማከማቻ መጋዘን ሊኖረው ይገባል፡፡

ሐ. የማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣ አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፣

መ. የማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆንአለበት፣

ሠ. የሙቀት እና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ በየመጋዘኑ መኖር ያለበት ሲሆን የመሣሪያው ትክክለኛነት በሚመለከተው አካል በየዓመቱ መፈተሽና መረጋገጥ አለበት፤

ረ. የመኖ ጥሬ ዕቃና ያለቀለት ምርት በመኖ መደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ መደርደር አለበት፣

ሸ. በመኖ መሸጫ ክፍል ዉስጥ በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የመኖ መመዘኛ

ዲጂታል ሚዛን መኖር አለበት፣

ቀ. አዲስ ለሚቋቋም የመኖ ማምረቻ ተቋምወይም ድርጅት ከማምረቻዉ የሚወጣ ማንኛዉም ፍሳሽ፣ቆሻሻ ወይም ተረፈ-ምርት በአካባቢዉ የተፈጥሮ ሀብት እና ነዋሪ ሕዝብ ላይ የሚያደርሰዉ አሉታዊ ተፅዕኖ ስለአለመኖሩ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት (Environmental Impact Assessment) ከመነሻዉ ተዘጋጅቶ ለባለሥልጣኑ ፈቃድ ሰጪ አካል ገቢ መደረግ አለበት፣

በ. ማንኛውም የመኖ ማምረቻ ድርጅት ቢያንስ የምርት ክፍል ዋና ኃላፊ እና የጥራት ቁጥጥር ክፍል ኃላፊነት መስፈርት የሚያሟሉ የመኖ ባላሙያዎችን በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

2. የመኖ አምራች ወይም ላኪ ድርጅት የግዴታ ውል የሚፈረምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)

ሀ. አዲስ የሚቋቋም የመኖ ማምረቻ ተቋም ወይም ድርጅት ከሆነ ከማምረቻዉ የሚወጣ ማንኛዉም ፍሳሽ፣ ቆሻሻ ወይም ተረፈ-ምርት በአካባቢዉ የተፈጥሮ ሀብት እና ነዋሪ ሕዝብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማያደርስ ሁኔታ የማካሄድ ግዴታ፣

ለ. በተዘረዘሩት የሙያ ዘርፎች ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

ሐ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣ የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል ግልጽ የማድረግግዴታ፡፡

## 2. የመኖ አስመጪ ድርጅት ማሟላት የሚገባዉ መስፈርቶች

1. ማንኛዉምሰውየብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡

ሀ. የመኖ ምርት መጫኛና ማራገፊያ መደላድል፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ መጋዘን፣ ያለቀለት ምርትና የመኖ ግብዓት ማከማቻ መጋዘን፣የምርት ጥራትና ደህንነት ፍተሻና ክትትል ክፍልሊኖረዉ ይገባል፤

ለ. የማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣ አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፤

ሐ. የማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ ምቹ ሁኔታ ያለዉመሆንአለበት፤

መ. የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም ምርት በመኖ መደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ

መደርደርአለበት፤

ሠ. በመኖ ጥሬ ዕቃ፣ በመኖ ንጥረ-ነገሮችወይም ግብዓቶች ወይም መኖ ምርት መጋዘንዉስጥ በሚመለከተውአካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የሙቀት እና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ በየመጋዘኑ መኖር አለበት፤

ረ. በመኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች መሸጫ ክፍል ዉስጥ አግባብነት ባለው ተቆጣጣሪ አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የመኖ መመዘኛ ሚዛንመኖር አለበት

ሸ. የመኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ቢያንስ የመኖ ሽያጭ ክፍል ኃላፊ ወይም የመጋዘን ሠራተኛበመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃትማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይገባዋል፤

ቀ. የመኖ አስመጪ ድርጅት ስለሚያስመጣው መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች በላኪውሀገርየታወቀና የተመዘገበ አምራች ስለመሆኑ እንዲሁም የመልካም አመራረት ምስክር ወረቀትበሀገሪቱ ተቆጣጣሪ መ/ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ እና ከላኪው ድርጅት ጋር የተደረገ የንግድ ስምምነትማስረጃወረቀትበቅድሚያ ማግኘትና ከብቃት መረጋገጫ ምስክር ወረቀት መጠየቂያማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

2. የመኖ አስመጪ ድርጅት የግዴታ ዉል የሚፈረምባቸዉ መስፈርቶች (Commitment paper)

ሀ. በተዘረዘሩት የሙያ ዘርፎች ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር ለማሠራትየተቀጣሪዎችንየተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

ለ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣ የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ህጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፡፡

## 3. የመኖ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ማሟላት የሚገባዉ መስፈርቶች

1. ማንኛዉምሰውየብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መሠረታዊ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡

ሀ. የመኖ ምርት መጫኛና ማራገፊያ መደላድል፣ የመኖ ጥሬ ዕቃ፣ ምርትና የመኖ ግብዓት ማከማቻ መጋዘን ሊኖረዉ ይገባል፤

ለ. የመኖ ማከማቻ መጋዘን ከአዕዋፍ፣ አይጥና ሌሎች የእህል በል እንስሳትና ተባይ ነፃ መሆን አለበት፤

ሐ. የመኖ ማከማቻ መጋዘን ለክትትል እንዲያመች በቂ ብርሃን የሚያስገባና ለመረማመድ

ምቹ ሁኔታ ያለዉ መሆን  አለበት፤

መ. የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም ያለቀለት ምርት በመኖ መደርደሪያ ጣዉላ ወይም ፕላስቲክ ፓሌት ላይ መደርደር አለበት፤

ሠ. በመኖ ጥሬ ዕቃ፣ በመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች ወይም መኖ ምርት መጋዘንዉስጥ በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ የሙቀት እና የእርጥበት መለኪያ መሣሪያ እንዲሁም የመኖ መመዘኛ ሚዛን በየመጋዘኑ መኖር አለበት፤

ረ. የመኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ቢያንስ የመኖ ሽያጭ ክፍል ኃላፊ ወይም የመጋዘን ሠራተኛ በመቅጠር የቅጥር ደብዳቤዉን ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጥያቄ ማመልከቻዉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይገባዋል፡፡

2. የመኖ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት የግዴታ ውል የሚፈረምባቸው መስፈርቶች(Commitment paper)

ሀ. በተዘረዘሩት የሙያ ዘርፎች ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

ለ. የተሟላ የሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣ የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ህጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፡፡

## 4. የመኖ ንግድ ሥራ ባለሙያ ማሟላት የሚገባው መስፈርቶች

1. ማንኛዉም የመኖ አምራች ድርጅት ቢያንስ የመኖ አመራረት ሂደት ኃላፊ እና የምርት ጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎችን ቀጥሮ ማሠራት አለበት፤

2. የመኖ ባለሙያዎችምበእንስሳትሳይንስናግጦሽመሬትአስተዳደርበመጀመሪያዲግሪየተመረቁሆነዉ በመኖ ዝግጅት፣ ቅንብርና ማኔጅመንት የተለየ ሥልጠና በመውሰድ ልዩ ሰርቲፊኬት ወይም ዲፕሎማ ሊኖራቸዉ ይገባል፤

3. ማንኛዉም የመኖ አስመጪ፣ ላኪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ለክምችትና ጅምላ ማከፋፈል ሥራ የቴክኒካዊ አሠራርንበኃላፊነት የሚመራ የመጋዘንና የሽያጭ ሠራተኛ የመኖ ባለሙያ ቀጥሮ ማሠራት አለበት፡፡ የሠራተኞች የትምህርት ዝግጅትና የብቃት መስፈርት የሚከተሉት ይሆናል፡-

ሀ. በድሮው የትምህርት ፖሊሲ መሠረት ከ12ኛ ክፍል በኂላ በኮሌጅ ደረጃ በሚሰጥሥልጠና በእንስሳት ሳይንስ በዲፕሎማ የተመረቀና በመኖ አያያዝና አጠቃቀምየልዩ ሥልጠና ሰርቲፊኬት ያለው፤

ለ. በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ መሠረት ከግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ (ATVET) በደረጃሁለት (II) የተመረቀና በእንስሳት መኖ ዓይነትና ባህሪያት እንዲሁም ክምችት፣ አያያዝ፣አጠባበቅናአጠቃቀም ላይ ያተኮረ ሥልጠና መዉሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ምስክር ወረቀት ሊኖረዉይገባል፡፡

ሐ. በመኖ ሥራ ዘርፍ የጥናት፣ የምርምርና የማማከር አገልግሎት ለመስማራት የሚያስችል ሙያ ሳይኖራቸው ድርጅት ለመክፈትና በማማከር ሥራ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት በዚህ አንቀፅከንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ድረስ የተጠቀሱትን የሙያ ዘርፍና የሥራ ልምድ ያላቸውን በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ መረጃና የቅጥር ደብዳቤ በዝርዝር ማቅረብ አለበት፡፡

4. የመኖ ንግድ ሥራ ባለሙያ የግዴታ ውል የሚፈረምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)

ሀ. በተዘረዘሩትየሙያዘርፎች ብቃት ያላቸውን ባለሙዎች በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ ዝርዝር መረጃ የማቅረብ፣

ለ. የተሟላየሥራ ሪከርድና ሠነዶችን አደራጅቶ መያዝ፣ የአገልግሎቱን አሰጣጥ ሂደት የተሟላ መረጃና ለምርመራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለሚመለከተው ህጋዊ አካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፡፡

## 5. በመኖ ንግድ የማማከር ሥራ ባለሙያ ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

1. በመኖ የንግድ ሥራ ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ባለሙያ በእንስሳትሳይንስ ወይም በእንስሳት ሳይንስ እና ግጦሽ መሬት አስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪና የአምስት ዓመትየሥራ ልምድ ወይም ሁለተኛ ዲግሪና የሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ወይም የሦስተኛ ዲግሪና ዜሮዓመት የሥራ ልምድ ሕጋዊ ማስረጃ ማቅረብ፣
2. በመኖ የንግድ ሥራ ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የማስተማር፣ የጥናት፣የምርምርናየማማከር ሥራ ቀደም ሲል በዚሁ በተጠቀሰው ዘርፍ ስለ መሥራታቸው በቂማስረጃ ማቅረብ፣
3. በመኖንግድሥራዘርፍየማስተማር፣የጥናት፣ የምርምርና የማማከር ዘርፍ ሙያ ሳይኖራቸውየማመከር አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ለመክፈትና በሥራው ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት በዚህ አንቀጽከንኡስ አንቀጽ ሀ እስከ ለ ድረስ የተጠቀሱትን የሙያ ዘርፍና የሥራ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ መረጃ በዝርዝር ማቅረብ አለባቸው፡፡

4. በመኖ ንግድ የማማከር ሥራ ባለሙያ የግዴታ ውል የሚፈረምባቸው መስፈርቶች (Commitment paper)

ሀ. በተዘረዘሩት የሙያ ዘርፎች ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር ለማሠራት የተቀጣሪዎችን የተሟላ ዝርዝር መረጃና የቅጥር ደብዳቤ የማቅረብ፣

ለ. የተሟላየሥራሪከርድናሠነዶችንአደራጅቶመያዝ፣ የአገልግሎቱንአሰጣጥሂደትየተሟላመረጃናለምርመራአስፈላጊበሚሆንበትጊዜለሚ መለከተውሕጋዊአካል ግልጽ የማድረግ ግዴታ፡፡

## 8. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማይጠየቅባቸዉ ልዩልዩ ሁኔታዎች

1. ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ማዉጣት ሳያስፈልግ የእንስሳት መኖን ወደ ሀገር ለማስገባት ወይም ወደ ዉጭ ሀገር ለመላክ የሚቻልበት ልዩ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡ ፡

ሀ. ለሳይንሳዊ ምርምር ጠቀሜታ የሚዉሉ የመኖ ናሙናዎች፣

ለ. ለዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች የቤት እንስሳት ፍጆታ የሚዉል መኖ፣

ሐ. በድርቅ፣ ጎርፍ፣ የመሬት ነዉጥና በአጠቃላይ ለችግር ጊዜ ደራሽ ዕርዳታየሚውልመኖ፣

2. የእንስሳትን ሕይወት ለመታደግደራሽ መኖ የሚያቀርቡ ግለሰቦች፣ ተቋማት ወይም ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያስፈልጋቸው፡-

ሀ. ከአካባቢው የግብርና ልማት ጽ/ቤት ወይም አርብቶ አደር ልማት ጽ/ቤት ወይም የእንስሳት ሀብት ልማት ኤጀንሲ ጽ/ቤት ወይም መስተዳድር አካል በአካባቢው ስለተከሰተው አደጋ የሚገልጽ ደብዳቤ በማቅረብ፣

ለ.ሕጋዊ የመኖ ንግድ ሥራ ፈቃድ ካለው ድርጅት በመግዛት

ሐ.የተከሰተው ችግር እውነተኛነት ሲረጋገጥ ከባለሥልጣኑ ወይም ውክልና ከተሰጠውአካል ለመኖው ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ የይለፍ ፈቃድ ደብዳቤ በማግኘት ወደ ተፈቀደውአካባቢ ማስተላለፍና ጥቅም ላይ ማዋል ይችላሉ፣

3. ከላይ በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖበተፈጠረዉ አጋጣሚ ችግርና ሁኔታ በማሳበብ የሚከናወን ሕገ-ወጥ ተግባር በማስረጃ ሲረጋገጥ ጉዳዩ በሕግ አግባብ የሚታይ ይሆናል፡፡

## 9. የንግድ አድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ

1. ማንኛዉም የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃወይም ግብዓት ንግድድርጅትባለስልጣኑን ሳያስፈቅድ የድርጅቱንየብቃትማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካገኘበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ማዛወር እንዲሁም የባለቤትነትለውጥ ማድረግ አይችልም፣

2. ማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ንጥረነገሮችወይም ግብዓቶች ንግድ ድርጅት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ሳያሳውቅ ሌሎች መጋቢወይም ተጨማሪ መጋዘኖችን መክፈት አይችልም፡፡

## 10. ምትክ  የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ስለ መስጠት

ቀደም ሲል የተሰጠዉ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ድርጅት ምትክ ሊያገኝ የሚችለዉ፡-

1. ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተበላሸበት ከሆነ ከነብልሽቱ የምስክር ወረቀቱንሲመልስና ምትክ እንዲሰጠዉ ሲጠይቅ፣ እና
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ከሆነስለመጥፋቱየሚገልፅ ማረጋገጫከሚመለከተው አካል ሲያቀርብና ምትክ እንዲሰጠዉ ሲጠይቅ እና
3. ለምትክአሰጣጡአስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል ብቻ ይሆናል፡፡

## 11. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት

ማንኛዉም የመኖ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊታደስለትየሚችለዉ፡

1. በወቅቱ ይዞት የሚገኘዉ የምስክር ወረቀት ታግዶ ወይም ተሰርዞ ካልሆነ፣ ወይም ድርጅቱ በራሱ ፈቃድ ሥራዉን ካላቋረጠ፣
2. ባለሥልጣኑ ለዚህ ሥራ ዘርፍ ያወጣቸዉ መመዘኛዎች የተጠበቁ ስለ መሆናቸው በባለስልጣኑ የምዝገባና ፈቃድ ባለሙያዎች በዓመታዊ የአሠራር ክትትል ሲረጋገጥ፣
3. ድርጅቱ ለዕድሳት አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል፣ በየዓመቱለዕድሳት በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ (ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 30 ባሉት ቀናት) ለዕድሳትጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ3 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ዉስጥ የምስክር ወረቀቱ በተለያየ ምክንያት ካልታደሰ በመጀመሪያው የጥቅምት ወር 25 በመቶ፣ በህዳር ወር 50በመቶበታህሳስ ወር እና ተከታታይ የበጀት ዓመቱ ወራት 75 በመቶ ከመደበኛው ክፍያ በተጨማሪ የገንዘብ ቅጣት በመክፈል ማሳደስ ይቻላል፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት ሳይታደስ የቀረ እንደሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖድርጅቱ በንግድ ሥራው መቀጠል ከፈለገ የተቀመጡትን መመዘኛዎች ስለማሟላቱ በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ሲረጋገጥ አዲስ የብቃት ማረጋጋጫ ምክር ወረቀት ማውጣት ይችላል፡፡

## 12. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ

ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይም ግብዓቶች ንግድ ድርጅት የተሰጠውንየብቃት

ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የዋናውን ቅጅ ሁልጊዜ በንግድ ቤቱ የሽያጭ ክፍል ዉስጥ በግልፅ በሚታይ ቦታ ላይ ከንግድ ፍቃዱ ጎን ለጎን መስቀልወይም ማስቀመጥ አለበት።

## ክፍል ሦስት

## የመኖ ማምረቻና ማከማቻ መጋዘን አሠራርና አስፈላጊ መስፈርቶች

### 13. የመኖ ንግድ ድርጅት ስለሚቋቋምበት አካባቢ ሁኔታዎች

ማንኛውም የመኖ ንግድ ድርጅት የሚቋቋምበት አካባቢ የሚከተሉትን ሁኔታዎችየሚያሚያላ መሆን አለበት። እነዚህም፡-

1. ለመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ አመቺ የመሠረተ ልማት አዉታሮች (ዉኃ፣ መብራት፣ የማመላለሻ መንገድ፣ ስልክ ወ.ዘ.ተ) ተሟልተዉ የተሠሩበት አካባቢ መሆን አለበት፣
2. የመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ መጋዘን ከነዳጅ ማደያ፣ ቄራ፣ የእንስሳት ማራቢያ ጣቢያ፣ ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ (ሆቴል፣ የጤና ተቋም፣ ትምህርት ቤት ወ.ዘ.ተ) ተቋማት ቢያንስ ከ300 እስከ 500 ሜትር ርቆ ወይም ለኢንዱስትሪ ዞን በተከለለ አካባቢ ሆኖ መኖን ሊበክሉ ከሚችሉ ከኬሚካል ማምረቻ ወይም መጋዘን፣ ከሲሚንቶ ወይም ብናኝና ሽታ ካላቸዉ ፋብሪካዎች ርቆ እንዲሁም ከተጠቀሱ ተቋማት በስተምሥራቅ አቅጣጫ መገኘት አለበት፣
3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7ከንዑስ አንቀጽ1 እስከ 5 የተመለከቱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነዉ በተጨማሪም የመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ መጋዘንና አካባቢዉ መኖን ሊበክሉ ከሚችሉ መርዛማ ይዘት ካላቸዉ ነገሮች እንዲሁም በመኖዉ ተመጋቢ እንስሳት ብሎም በእንስሳት ምርት ዉጤት ተመጋቢ ህብረተሰብ ጤና እና ደህንነት ላይ ቀጥተኛ ወይም የጎንዮሽ ጉዳት ለሚያስከትሉ ነገሮች ተጋላጭ ያልሆነ አካባቢ መሆን ይገባዋል፣

### 14. የመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ ግንባታ አሠራር

1. የመኖ ማምረቻ ፋብሪካ የሚደራጅበት ቦታ ከሽታና ብናኝ የፀዳ አካባቢ ሆኖከማምረቻዉየሚወጣቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓት ሊኖረዉ ይገባል፤
2. የመኖ ማምረቻ ፋብሪካ የጥሬ ዕቃ መፈተሻ፣ ማራገፊያ እና መጫኛ መደላድል፣ መረከቢያናማከማቻ መጋዘን ሊኖረዉ ይገባል፤
3. የመኖ ማምረቻ ፋብሪካ የማምረቻ ሂደት (ማበጠሪያ፣ መፍጫ፣ መደባለቂያ፣ ማድረቂያ፣ መመዘኛ፣ማሸጊያ፣የመግለጫ ጽሁፍ ወ.ዘ.ተ) ሥራዎች የሚከናወኑበት የአሠራር መስመሮች በግልጽመቀመጥና መታየት አለባቸዉ፤
4. የግንባታዉ አሠራር ለዚህ ተግባር ለሚዉሉ ሕንፃዎች በሚወጣ ደረጃና መስፈርት መሠረትየማምረቻ ወይም የማከማቻ ተቋም ተለይቶአግባብ ባለዉ የምህድስና ተቋም

የተረጋገጠ መሆንይገባዋል፤

5. የመኖ ምርት ማከማቻ መጋዘን በምርቱ ጥራትና ጤናማነት ላይ ተፅእኖ በማያሳድር መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፤
6. የመኖ ምርት ማከማቻ መጋዘን ስፋት በምርቱ ብዛትና የክምችት ቆይታ ጊዜ ጋር በተጣጣመሁኔታ በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች የሚወሰን ሆኖ የማከማቻ መጋዘንናየመሸጫ ክፍል ግን ተለያይተዉ መሠራት ይገባቸዋል፤
7. የመኖ ምርት ማከማቻ መጋዘን ከፍሳሽ፣ እርጥበትና ሌሎች የመኖን ምርት ለብልሽት ሊያጋልጡ ከሚችሉ ነገሮች ለመጠበቅ በምርት መደርደሪያ ዕቃ ወይም ከጣዉላወይምከፕላስቲክ የተሠራ መደርደሪያ ፓሌት ላይ መደርደርና መጠበቅ ይኖርበታል፤
8. የመኖ ምርት ማከማቻ መጋዘን ወለል ዉኃ የማያቁርና በሸካራ ሊሾ የተሰራ ሆኖ ግድግዳዉከሸክላ ወይም ብሎኬት ወይም ቆርቆሮ እና ከመሳሰሉት የተሠራና በሩ እና መስኮቱ እንዲሁም የአየር መዘዋወሪያ ቬንቶችበወንፊት ሽቦ የተሸፈኑና አይጥ፣ ወፍ እና ሌሎች እህል በል የሆኑ ነፍሳትን የማያስገባ መሆን አለበት፤
9. የመኖ ምርት ማከማቻ መጋዘን በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ መዋል ከማይችሉ መኖ እና የመኖ ግብዓቶች የፀዳ መሆን ይገባዋል፡፡ ጥቅም ላይ መዋል የማይገባቸዉ መኖ እና የመኖ ግብዓቶችበአግባቡ ማስወገድ እስከሚቻልበት ወቅት ድረስ የተለየ የማከማቻ ክፍል ወይም መጋዘን ዉስጥ በተለየ ሁኔታ በጽሑፍ ተገልጾ መጠበቅ ይገባል፤የመኖ ማምረቻ ወይም ማከማቻ መጋዘን የድርጅቱ ሠራተኞች መገልገያ መጸዳጃ፣ መታጠቢያናየልብስ መቀየሪያ ክፍሎች እንዲሁም የእሳት አደጋ መከላያ አነስተኛ መሣሪያ ሊኖሩት ይገባል፡፡

## 15. በመኖ ማከማቻ መጋዘን ዉስጥ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችና ቁሳቁሶች

1. መኖ እና የመኖ ግብዓቶች በመጋዘን ዉስጥ ለአጭር ወይም ለረጅም ጊዜ በሚከማቹበት ወቅት ከማንኛዉም ብልሽት ለመጠበቅ ከወለል በላይቢያንስ 10 ሳ.ሜ ከፍ ብለው በሚሠሩ መደርደሪያ ፓሌቶች ላይ፣ ከግድግዳ 50 ሳ.ሜ ርቀው እና ከጣራ በታች 50 ሳ.ሜ ዝቅ ብለው ከነመያዣቻዉ መከማቸት አለባቸው፤
2. በመጋዘኑ ዉስጥ የሙቀትና የዕርጥበት መለኪያዎች (ቴርሞ እና ሀይግሮ ሜትር) በቅደም ተከተላቸዉ መኖርና በአግባቡ ማስቀመጥይገባል፡፡ የዉስጥ ሙቀት የመኖምርት ለብልሽት የሚዳርግበት ደረጃ የሚደርስ ከሆነ እንደየአካባቢዉ ሁኔታ የዉስጥሙቀትን ማቀዝቀዝ የሚችል ከመጋዘኑ ስፋት ጋር ተመጣጣኝ ቬንትሌተር ማስገባትይገባል፤
3. የመኖ እና የመኖ ግብዓቶች ሽያጭ ትክክለኛ ክብደት በሚያሳይ ሚዛን መሆን አለበት፣

4. የሚዛኑ ትክክለኛነትም በሚመለከተው አካል በየዓመቱ በመፈተሽና በማረጋገጥ ሲሆን የፍተሻዉ ማረጋጋጫ ወረቀት በሚዛኑ አጠገብ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 16. የመኖ እና መኖ ግብዓት መያዣ ወይም ማሸጊያ ዕቃዎች ሁኔታ

1. የመኖ እና መኖ ግብዓት መያዣ ዕቃዎች፣ ማሸጊያዎች፣ መደርደሪያዎች ሁሉ ከዝገትእንዲሁም መኖን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች የፀዱ መሆን አለባቸው፤
2. የመኖ እና መኖ ግብዓት መያዣ ዕቃዎች፣ ማሸጊያዎች፣ ለዚህ ተግባር እንዲዉሉ በመኖ ደረጃዎች ዝግጅት በሚወሰነዉ መሠረት በዝርዝር የሚገለጽ ቢሆንም ማንኛዉም መያዣ ወይም ማሸጊያ ከቃጫ ወይም ከፕላስቲክ ክር የተሠራና ምርቱን በማያፈስ ሁኔታ መሰፋት አለበት፤
3. ማንኛዉም የመኖ እና መኖ ጥሬ ዕቃወይም ግብዓት መያዣ ከፕላስቲክ ወይም ከዝገት ነፃ ከሆነ ዕቃ የተሠራ መሆን አለበት፡፡ የመኖ መያዣ ከፀረ-ተባይና የአፈር ማዳሪያ፣ የቁሳቁስ ማፅጃ ኬሚካሎች፣ ናፍታ፣ ከነዳጅና ቅባት ነገሮች እንዲሁም ከበርበሬ ወይም ከተላያዩ ቅመማቅመም ጋር የተነካካ መሆን የለበትም፤
4. ማንኛዉም የመኖ እና መኖ ጥሬ ዕቃግብዓት መያዣ ዕቃ ለመኖ መያዣነት ብቻ ተለይቶ በጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡ በተደጋጋሚ ለመያዣ አገልግሎት የሚዉለዉም ለመኖ ብቻ ሆኖ ለሌሎች ዕቃዎች ወይም የንግድ እህሎች መያዣ አገልግሎት መዋል የለበትም፤
5. ማንኛዉም ፈሳሽ የመኖ እና መኖ ጥሬ ዕቃ ወይም ግብዓት ከአቧራና ብናኝ ነገር ለመከላከል እንዲቻል በፕላስቲክ ወይም ከዝገት ነፃ በሆነ መያዣ ዉስጥ መያዝ አለበት፡፡ መያዣዉም ከፀረ-ተባይና የቁሳቁስ ማፅጃ ኬሚካሎች፣ ናፍታ፣ ከነዳጅና ቅባት ነገሮች ጋር የተነካካ መሆን የለበትም፡፡

## 17. በመኖ እና መኖ ጥሬ ዕቃወይም ግብዓት መያዣ ላይ መኖር ስለሚገባዉ ገላጭ ጽሑፍ

1. ማንኛዉም ለንግድ አገልግሎት የሚዉል የእንስሳት መኖ በማሸጊያዉ ላይገላጭ ጽሑፍካልተደረገበት በስተቀር ለገበያ ሊቀርብ ወይም ሊዘዋወርና ለሽያጭ ሊሰራጭ አይችልም፣
2. የመኖ ገላጭ ጽሑፍ በእንግሊዘኛ ወይም በአማርኛ ቋንቋ (ወደ ዉጪ የሚላክ መኖ በተቀባይ ሀገርጥያቄ መሠረት ይሆናል) በመኖ መያዣዉ ላይ ግልጽ፣ ጉልህናበማይለቅ ቀለም መጻፍአለበት፡፡ የመኖ ገላጭጽሑፍዝርዝር ይዘት የሚከተሉትንየሚያካትት መሆን አለበት፡-

ሀ. የመኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃወይምግብዓት አምራች ወይም አከፋፋይ ድርጅትስምናሙሉ አድራሻ የሚገልጽ፤

ለ. የመኖዉ ወይም የመኖ ግብዓት የንግድ ወይም የብራንድ ስም የሚገልጽ፤

ሐ. መኖዉ ወይም የመኖ ግብዓት የተመረተበት ቀንና ዓመተ ምህረት፣

መ. የመኖዉ ምርት መለያ ቁጥር (Batch number)፣

ሠ. የመኖው መጠቀሚያ የሚያበቃበት ጊዜ (ወርና ዓ.ም)፣

ረ. የመኖዉ ንጥረ ነገሮች ዝርዝር ይዘት ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተላቸዉ

ተ. የመኖው ምርት የተጣራ ክብደት (በግራም፣ በኪ.ግ)

ቸ. መኖው ለየትኛዉ የእንስሳት ዓይነት፣ የዕድሜ ክልል፣ የምርት ዓይነትና ደረጃ እንደተዘጋጀ የሚገልጽ (የወተት ዳልጋ ከብት፣ የዳልጋ ከብት ማድለቢያ፣ የበግ ወይም የፍየል ማድለቢያ፣ ለዕንቁላል ጣይ ዶሮ፣ ለሥጋ ዶሮ፣ ለጫጩት፣ ለጥጃ ወዘተ) በማካተት የአጠቃቀምና አያያዝ ሁኔታ የሚገልፅ መረጃ በግልጽ መስፈር አለበት፤

ኘ. መኖዉ ወይም የመኖ ግብዓት ስለሚጓጓዝበትና ስለሚከማችበት ሁኔታና መደረግ ስለሚገባዉ ጥንቃቄ ወይም ማስገንዘቢያ ወይም ማስጠንቀቂያ በገላጭጽሑፍላይ በማካተት በግልጽ በሚነበብና በማይለቅ ቀለም መስፈር ይገባዋል፡

## ክፍል አራት
## የመኖ ንግድ ድርጅት ሠራተኞች ሙያዊ ብቃት

### 18. ስለ መኖ የቴክኒክ ሠራተኛ የሙያ ብቃት ደረጃዎች

1. ማንኛዉም የመኖ አምራች ድርጅት ቢያንስ የመኖ አመራረት ሂደት ኃላፊ እና የምርት ጥራት ቁጥጥር ባለሙያዎችን ቀጥሮ ማሠራት አለበት፤
2. ማንኛዉም የመኖ አምራች ድርጅትባለሙያዎች በእንስሳት ሳይንስና ግጦሽመሬት አስተዳደር በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁ ሆነዉ በመኖ ዝግጅት፣ ቅንብርና ማኔጅመንት የተለየ ሥልጠና በመውሰድ በዚሁም ልዩ ሰርተፊኬት ወይም ዲፕሎማ ሊኖራቸዉ ይገባል፤
3. ማንኛዉም የመኖ አስመጪ፣ ላኪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ለክምችትና ጅምላ ማከፋፈል ሥራ የቴክኒካዊ አሠራርንበኃላፊነት የሚመራ የመጋዘንና የሽያጭ ሠራተኛ ቀጥሮ ማሠራት አለበት፡፡
4. ከላይ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 3 የተጠቀሱ የመኖ አስመጪ፣ ላኪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅትሠራተኞች የትምህርት ዝግጅትና የብቃት መስፈርት በሚከተለው መሠረት ይሆናል፡-

   ሀ. በድሮው የትምህርት ፖሊሲ መሠረት ከ12ኛ ክፍል በኂላ በኮሌጅ ደረጃ በሚሰጥ

ሥልጠናበእንስሳት ሳይንስ በዲፕሎማ የተመረቀና በመኖ አያያዝና አጠቃቀም የልዩ ሥልጠና ሰርቲፊኬት ያለው፤

ለ. በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ መሠረት ከግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ (ATVET) በደረጃ ሁለት (II) የተመረቀና በእንስሳት መኖዓይነትና ባህሪያት እንዲሁም ክምችት፣ አያያዝ፣ አጠባበቅናአጠቃቀም ላይ ያተኮረ ሥልጠና መዉሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃና ዲፕሎማ ሊኖረዉ ይገባል፡፡

## 19. የመኖ ንግድ ድርጅት የቴክኒክ ሠራተኛ እና ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት

1. የመኖንግድ ድርጅት የቴክኒክ ሠራተኛ ወይም ባለሙያ ድርጅቱ በሚያመርተው፣ በሚያስመጣውና በሚያከፋፍላቸው የእንስሳት መኖ እና የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች ላይ ለሚከሰቱ የጥራትና ደህንነት ችግር ሁኔታ መከታተልና ጉዳት ከመከሰቱ በፊት ችግሩን ለባለ ድርጅቱ በአፋጣኝ ማሳወቅ አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ1የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የድርጅቱ ባለቤት ለተከሰተው ችግር በአፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ የቴክኒክ ሠራተኛው ወይም ባለሙያው ለባለስልጣን መ/ቤቱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤
3. ከመኖ ደህንነትና ጥራት መጓደል ጋር ተያይዞ ለሚከሰት ማንኛውም ችግር ከድርጅቱ በተጨማሪ የቴክኒክ ሠራተኛው ወይም ባለሙያው ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## መኖ ወደ ሀገርውስጥ ስለማስገባትና ወደ ውጭ ሀገር ስለ መላክ

## 20. መኖና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮችንወይምግብዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥስለማስገባት

1. ማንኛውም የመኖ ንጥረነገሮችወይም ግብዓቶች ንግድ ድርጅት ከባለሥልጣኑ ፈቃድሳያገኝ መኖ ወይምየመኖ ግብዓትወደ ሀገርውስጥ ማስገባት አይችልም፤
2. ማንኛውም ወደ ሀገር ውስጥየሚገባ መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገርወይምግብዓት በዚህ የመኖ ጥራት ደረጃዎች ምዝገባና ፈቃድ አሠራር መመሪያ መሠረት መመዝገብ አለበት፤
3. ማንኛውም ወደ ሀገር ውስጥየሚገባ መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገርወይምግብዓት በላኪው ሀገር የተመዘገበናከሚመለከተው የላኪው ሀገር ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የመልካም አመራረት ማረጋገጫ የምስክርወረቀትባለውድርጅትየተመረተስለመሆኑመረጋገጥ አለበት፤
4. ማንኛውምመኖ የመኖ ግብዓት ወደሀገርየሚገባው ሕጋዊ የመኖ ማስገቢያ ፈቃድበተሰጠዉየመኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶችአስመጪ ድርጅት ብቻ ነዉ፤

5. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአስቸኳይ አደጋና ለእንስሳት ሕይወት አድን ተግባር ሲባል የዕርዳታ ሰጪ ድርጅት ከውጪ መኖ ለመስገባት ጥያቄሲያቀርብ በአንቀጽ 8 ንኡስአንቀጽ 2 መሠረትየጥራትና ደህንነት መስፈርቶችን በማረጋገጥ የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጠዋል፤

6. ማንኛውምወደሀገርለሚገባ መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገርወይምግብዓት የማስገቢያ ፈቃድ የሚሰጠዉ ሀገሪቱ ባወጣችዉ ወይም የተቀበለቻቸዉ ዓለም አቀፍ የመኖ ጥራት ደረጃዎችን አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነዉ፤

7. ማንኛውምወደሀገርየሚገባ መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች የሚከተሉት የማረጋገጫ ሰነዶችን የያዘ መሆን አለበት፡፡

ሀ. የመኖውን ጤናማነትና ደህንነት የሚገልጽ የጤና ምስክር ወረቀት (Sanitary orphytosanitary Certificate)፤

ለ. የመኖዉ ንጥረ ነገሮች ዝርዝር ይዘት ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተላቸዉ

ሐ. የምርት ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት (Certificate of Batch Analysis)፤

መ. የመልካም አመራረት ተሞክሮ ሰርተፍኬት (Good Manufucturing Practices (GMP)Certificate) ፤

ሠ. ዘረመሉ ከተለወጠ ግብዓት ነፃ ስለመሆኑ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት(Genetically ModifiedOrganism (GMO) Free Certicate) ፤

ረ. ከአመንዣኪ እንስሳት ፕሮቲን ምርት ዉጤት ነፃ ስለመሆኑ የማረጋገጫ ሰርቲፊኬት(Ruminant Origin Protein Free Certificate)፡፡

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ረየተመለከተው ከአመንዣኪ እንስሳት ፕሮቲን ምርት ነፃ የመሆን መስፈርት ለቤት እንስሳት ምግብ (Pet Animals Food) የሚውለውን ምርት አያካትትም፤

9. ከልዉጥ ሕያዉ ወይም ዘረመሉ ከተለወጠ ግብዓት የተቀመመ ወይም የተቀነባበረ መኖ ወይም የመኖ ግብዓት (Processed from GMO Products) ወደ ሀገር ለመስገባት ፍላጎት ያለው ድርጅት በአዋጅ ቁጥር 655/2001 አንቀጽ 5እና 20 መሠረት በደንና አካባቢ ጥበቃ ሚኒስቴር ፈቃድና ቁጥጥር አሠራር ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

10. ማንኛውምወደሀገርውስጥየሚገባ መኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገሮችወይምግብዓቶች መያዣ ገላጭ ጽሑፍበአንቀጽ 17 ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አሟልቶ መቅረብ አለበት፡፡

## 21. በመኖወይምየመኖ ንጥረ-ነገሮች ጤና ሰርተፊኬት ላይ መካተት ያለባቸው መረጃዎች

ማንኛውም የመኖ ጤና ሰርተፊኬት አግባብ ባለው ተቆጣጣሪ አካል የተሰጠና ከ3 ወር በላይ ያልቆየ ኦርጅናል ሰነድ ሆኖ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች ያካተተ መሆን አለበት፡-

1. የመኖ ጤና ሰርተፊኬት ሰጪ ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤
2. የመኖ ጤና ሰርተፍኬቱ መለያ ቁጥር፤
3. የመኖ ጤና ምርመራ የተደረገበት ቀንና ዓመተ ምህረት፤
4. የመኖ ጤና ሰርተፍኬት ያረጋገጠዉ አካል ሙሉ ስም፣ አድራሻና ማህተም
5. የመኖ ላኪውና የተቀባይ ድርጅቱ ስምና ሙሉ አድራሻ፤
6. የ መኖ ዓይነት ዝርዝርና መጠን በኪ.ግ ወይም በቶን፤
7. የመኖ ላኪዉ ኢንቮይስ (ደረሰኝ) ቁጥር፤
8. የመኖ ጤና ሰርተፊኬቱን ያረጋገጠዉ አካል ሙሉ ስምና ኃላፊነት፣አድራሻናየጤና መርማሪ ድርጅቱ ማህተም በግልጽ መስፈር አለበት።

## 22. በመኖ ወይም የመኖ ግብዓቶች ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት ላይ መካተት ያለባቸውመረጃዎች

ማንኛውም የመኖ ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት ዋናው ቅጂ ሆኖ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎችን ማካተት አለበት፡-

1. ምርመራውን ያካሄደው ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ
2. የመኖው አምራች ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤
3. የመኖው መጠሪያ ስም፣ የተመረተበት ቀንና ዓ.ም እንዲሁም የመጠቀሚያው ጊዜ ወርና ዓ.ም፣
4. የምርት ባች መለያ ቁጥር (Batch number)፤
5. የተካሄደው ዝርዝር የምርመራ ዓይነት፣ የተገኘው ውጤትና የተጠቀሙበት የምርመራ ዘዴ፣
6. ምርመራ የተደረገበት ቀንና ዓ.ም፤
7. የምርመራዉን ውጤት ያረጋገጠዉ አካል ሙሉ ስም፣ አድራሻና የመርማሪ ድርጅቱ ማህተም በግልጽ መስፈር አለበት።

## 23. መኖ እና የመኖ ንጥረ ነገሮችወይምግብዓቶች ከሀገር ስለማስወጣት

1. ማንኛውም ሰውከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና የላኪነትወይም ማዉጫ ፈቃድ ሳያገኝ መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገርወይም ግብዓት ወደ ውጭ ሀገር መላክ አይችልም፤
2. ማንኛዉም ወደ ወጭ ሀገር የሚወጣ መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገርወይም ግብዓት በባለሥልጣኑ የተመዘገበናአምራች ድርጅቱም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠዉ ስለመሆኑ መረጋገጥ አለበት፤
3. ማንኛዉም ወደ ወጭ ሀገር የሚወጣ መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገርወይም ግብዓት የጤና

ሰርተፊኬት ወይም የሳኒተሪ ወይም የፋይቶ ሳኒተሪ ሰርተፍኬት ማግኘት ይኖርበታል ሆኖም አንድ የጤና ሰርተፊኬት የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ጭነት (Consignment) ብቻ ነው፤

4. ማንኛውምወደዉጭ ሀገርየሚወጣ መኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገርወይምግብዓት ፈቃድ የሚሰጠዉ ሀገሪቱ ባወጣችዉ ወይም በተቀበለቻቸዉ ዓለም አቀፍ የመኖ ጥራት ደረጃዎች እና ተቀባይ ሀገር የሚያቀርበዉን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡

## ክፍል ስድስት

## መኖና የመኖ ግብዓቶችን ስለ ማከማቸት፣ማከፋፈልና ማጓጓዝ

### 24. የመኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች አከመቻቸትና አያያዝ ሁኔታ

1. ማንኛውም የመኖ ንግድ ድርጅት የሚያከማቸውን መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶች እንደምርቶቹልዩ ባህሪይና ዓይነት ማከማቸት አለበት፣
2. የመኖ ንግድ ድርጅትመኖውንወይም የመኖ ግብዓቶችን ሊበክሉ ከሚችሉ ፀረ-ተባይና ሌሎች ኬሚካሎች ጋር አብሮማከማቸት የለበትም፣
3. የተበላሹ፣ የተከለሱ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችን እስኪወገዱ ድረስ በአግባቡ ተቆጥረውና ተመዝግበው ከሌሎች ተለይተው ጥቅም ላይ እንደማይውሉ የሚገልፅ ፅሁፍ በመለጠፍ ለብቻ መቀመጥ (መደርደር) አለባቸው፣
4. የመኖና የመኖ ግብዓቶች ንግድ ድርጅትየመጠቀሚያ ጊዜያቸዉሊያበቃ አጭር ጊዜ የቀራቸውንመኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገርወይምግብዓቶችን በቅድሚያ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ማድረግ አለበት፣
5. የመኖ ወይም የመኖ ግብዓቶች ማከማቻ መጋዘን ንፁህ፣ ደረቅ፣ ከመደበኛ የክፍል ሙቀት ብዙ ያልበለጠ፣ ከተባይና እህል በል ተባይወይምእንስሳት ነፃ መሆን አለበት
6. በየመጋዘኑ እና በተለያዩ የመጋዘን ክፍሎች የምርት ዓይነት፣ ምርቱ ያለበት ሁኔታ (status) እና ሌሎችስለ መኖ ወይም መኖ ግብዓቶች ዝርዝር መግለጫ መረጃዎች በየጊዜውበማደስ መለጠፍአለባቸው፡፡
7. ማንኛውም የመኖ ወይም የመኖ ግብዓቶች ማከማቻ መጋዘን እንደምርቱ ዓይነትና ባህሪይ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ከአንቀፅ 16 እስከ 18 በተዘረዘሩት መሠረት የማከማቻ መጋዘንመስፈርቶችን ያሟላ መሆን ይገባዋል፡፡

## 25. መኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገሮችወይም ግብዓቶችን ስለ ማከፋፈል

1. ማንኛውም የመኖጅምላአከፋፋይድርጅትመኖንመግዛትየሚችለው በባለስልጣኑ የብቃትማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠውና ከተመዘገበ የመኖ አስመጭ ወይም ከአገር ውስጥ መኖአምራች ድርጅት ብቻ መሆን አለበት፣
2. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶች ንግድ ድርጅት በክምችትና በአጓጓዝ ሂደት ወይምበማንኛውም ምክንያት ብልሽት ያልደረሰበትና ተገቢውን የጥራትና የደህንነት ደረጃ የጠበቀ መኖ ብቻ ማከፋፈል አለበት፣
3. ማንኛውም መኖ አምራች ድርጅት ለገዢው የውስጥፍጆታ ካልሆነ በስተቀር ለንግድ የሚውል መኖን ሕጋዊ ፈቃድ ለሌለው ግለሰብ ወይም ድርጅት መሸጥ አይችልም፣
4. መኖ ወይም የመኖ ግብዓት አከፋፋይ ድርጅት ለሚያከፋፍላቸው መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይም ግብዓቶች የግዥና የሽያጭ ደረሰኝ ሊኖረው ይገባል፣
5. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ግብዓት አከፋፋይ ድርጅት የሚያከፋፍለው መኖ ወይም የመኖንጥረ-ነገሮችወይም ግብዓቶች በአንቀፅ 20 ላይ ስለ ማሸጊያ ገላጭ ፅሁፍ የተቀመጠውን መስፈርትየሚያሟላና መጀመሪያ ከነበረው መልክና ሁኔታምንም ዓይነት ለውጥ ወይም መቀነስ ወይምመከለስ ያልተደረገበትና ብልሽት ያልደረሰበት መኖ መሆን ይገባዋል፡፡

## 26. መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችንወይምግብዓቶችንስለማጓጓዝ

1. ማንኛውንምመኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገሮችወይም ግብዓቶች በአቧራ፣ ኬሚካል፣ ነዳጅና ቅባት፣ በባዕድ ነገሮችወ.ዘ.ተ ለብክለት በሚያጋልጥ ሁኔታ ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፣
2. የመኖ ወይም መኖ ንጥረ-ነገሮችወይም ግብዓቶች ማጓጓዣ መሣሪያ ንፁህ፣ ደረቅና ምርቱን ከማናቸውም ብክለትየሚከላከል ስለመሆኑ በውስጥ የጥራትና ደህንነት ባለሙያ መረጋገጥ አለበት፣
3. መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች የሚጫኑትና የሚራገፉት ማንኛውም እርጥበት ምርቱን በማይነካበት ሁኔታ መሆን አለበት፣
4. ከመኖው ወይም መኖ ንጥረ ነገሮችወይምግብዓቶች ጋር የሚቃረን ባህሪይ ያለው ወይም ምርቱን ሊበክል ከሚችል ማንኛውም ዓይነት ዕቃ በተጫነበት ማጓጓዣ መጫንና ማጓጓዝ የተከለከለ ነው፣
5. ተገዝቶ ወይም ለሽያጭ የሚጓጓዘው መኖ ወደ ሚፈለግበት የማከማቻ መጋዘን በአጭር ቀንና ጊዜ ውስጥ በጥንቃቄ እንዲደርስ መድረግ አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት
## የአስተዳዳራዊ እርምጃዎች አወሳሰድ

### 27. ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት

1. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይም ግብዓቶች ንግድ ድርጅት ይህን መመሪያና ሌሎችድንጋጌዎችንየጣሰ እንደሆነና ጥፋቱበወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑእንደተጠበቀሆኖ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን የሚያሳግድ፣ የሚያሰርዝ ወይም ሌሎች ከባድአስተዳዳራዊ እርምጃዎችን የሚያሰወስድ ካልሆነ በስተቀር ባለስልጣኑ እንደ አግባቡ የቃልወይም የፅሁፍ ማስጠንቀቂያሊሰጥ ይችላል፣
2. በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ድርጅቱ አስፈላጊውን ማስተካከያ ካላደረገ በዚህ መመሪያከአንቀጽ 31 እስከ 33 በዝርዝር በተመለከተው መሠረትተገቢውን እርምጃ ሊወሰድበትይችላል፡፡

### 28. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትዕገዳ

ማንኛዉም መኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገሮችወይም ግብዓቶች ንግድ ድርጅት ከሚከተሉትምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛሆኖከተገኘ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልግ ባለስልጣኑጉድለቶች ወይም ጥፋቶች እስኪስተካከሉድረስ የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀቱንሊያግድበትይችላል፡፡

1. ሕጋዊና ወቅታዊ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትና የንግድ ፈቃድ ከሌለው ድርጅት መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችንወይም ግብዓቶችን ከገዛ ወይም በማንኛውም መንገድ ከተቀበለ ወይም የሥራና የንግድ ፈቃድ ለሌው ድርጅት ሸጦ ከተገኘ፣
2. ለባለስልጣኑ ሳያሳውቅ የመኖ ንግድ ድርጅቱን የቦታና አድራሻ ለዉጥ ካደረገ፣
3. በኢትዮጵያ የወጣውን ወይም ሀገሪቷ የተቀበለችውን የጥራት ደረጃዎች የማያሟላ መኖ፣ የመኖ ንጥረ ነገርወይም ግብዓት በመኖ ንግድ ገበያ ላይ አውሎ ከተገኘ፣
4. መኖ ወይም መኖ ንጥረ-ነገሮችንወይም ግብዓቶችን ለማጓጓዝ የወጡትን መስፍርቶች በማይጠብቅ ሁኔታ ካጓጓዘ፣ ካከማቸ ወይም ሲሸጥ ከተገኘ፣
5. ባለሥልጣኑ በድርጅቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርጋቸው ማንኛውም የኢንስፔክሽንሥራዎች እንዳያከናውን እንቅፋት ከሆነ ወይም ችግር የፈጠረእንደሆነ፣
6. በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ 7 ንዑስ አንቀጽ1እስከ 3 ከተጠቀሱት መስፈርቶች መካከል ጉድለትና ጥፋት ሲገኝበት፣
7. በባለሥልጣኑ ከሁለት ጊዜ በላይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ድርጅቱ የማያስተካክል ከሆነ ወይም የኅብረተሰቡንና የአካባቢውን ጤና በማይጎዳ ሁኔታ እንዲመረት መመሪያው ባስቀመጠው መሰረት የምርት ሂደቱን ካልፈፀመ፣

## 29. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትስለመሰረዝ

ማንኛዉምመኖ ወይም የመኖ ንጥረ- ነገርወይም ግብዓት ንግድ ድርጅትከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊሰርዝበት ይችላል፡-

1. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከመመሪያው አሠራር ውጭ በሆነ መንገድየተገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ፣
2. የብቃት ማረጋገጫ ወረቀቱን በማናቸውም መንገድ ለሌላ ወገን አስተላልፎ ከተገኘ
3. ማንኛውንም መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችከሚገባው ይዘት በላይ ክብደት ለመጨመር ወይምበቀለም ማስዋቢያ ወይም ሌላ ባዕድ ነገር ጨምሮና ከልሶ ወይም አስመስሎ በማቅረብ ሥራላይ ከተገኘ፤
4. ድርጅቱ የብቃትማረጋገጫምስክርወረቀትካወጣበትየምርት ዓይነት ውጪ ሲያመርት፣ ሲያስመጣ፣ ወደ ውጭ ሲልክ ወይም ሲያከፋፍል ከተገኘ፣
5. መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችን ማስመዝገብ ሲገባው ያላስመዘገበ፣ የተበላሸ፣የአገልግሎት ጊዜ ያለፈበትን፣ ገበያ ላይ እንዳይውል የታገደ፣ ስለምርቱ ሁኔታ ገላጭ ጽሑፍ የሌለው ወይም አሳሳች ገላጭ ጽሑፍ ያለውን የያዘ፣ የሸጠ ወይም ያከፋፈለ፣ የከለሰ፣ አስመስሎ ያቀረበ፣ በሕገወጥ መንገድ ንግድ ውስጥ የገባ፣
6. ከአምራቹ ድርጅት የውል ስምምነት ሳይኖረው በቅድሚያ የታሸገ መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችን እንደገና ከፋፍሎ በማሸግ ወይም ሌላ ገላጭ ጽሑፍ በማድረግ ከሸጠ፣
7. የመኖ ንግድ ድርጅቱ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 14 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በወቅቱ ካላሳደሰ፣
8. የመኖ ንግድ ድርጅቱ በባለስልጣኑ የተጣለበትን ዕገዳ በመተላለፍ ሥራውን ሲያከናውንከተገኘ፣
9. ድርጅቱ ስለ ብቃት ማረጋጋጫ ዕገዳ በአንቀፅ 31 ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶችበመተላለፍ ተመሳሳይጥፋቶችን በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ ፈፅሞከተገኘ፣

## 30. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለባለሥልጣኑ ስለመመለስ

1. ማንኛውም የመኖ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ዓይነት እና የቦታ ለውጥ ሲያደርግና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ጠይቆ ተቀባይነት ሲያገኝ ነባሩን የሥራ ፈቃድ ለባለሥልጣኑ መመለስ አለበት፣
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰረዘ፣ ከታገደ፣ በተቀመጠው የዕድሳት ጊዜ ገደብ ሳይታደስከቀረ ወይም በራሱ ፈቃድ የንግድ ስራውን ካቋረጠድርጅቱ ነባሩን ፈቃድ በአሥር

የሥራ ቀናትውስጥለባለሥልጣኑ መመለስ አለበት፡፡

## 31. የብቃት ማረጋገጫምስክር ወረቀትዕገዳ ስለማንሳትና የተሰረዘውን ስለመተካት

1. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት መኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገሮችወይምግብዓቶች ንግድ ድርጅት የተጣለበት ዕገዳ ሊነሳለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ድርጅቱ ለዕገዳ ያበቃውን ጥፋት ካረመ ወይም ካስተካከለ ዕገዳው ሊነሳለት ይችላል፣
2. ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰረዘበት መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች ንግድ ድርጅት የተሰረዘ ፈቃድ ሊተካለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝና ድርጅቱ ለስረዛ ያበቃውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ በማረምና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው ጥያቄ ሲያቀርብ የተደረገው የተሟላ ማስተካከያ በባለሙያዎች ተረጋግጦ በተሰረዘው የምስክር ወረቀት ፋንታ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊሰጠው ይችላል፡

## 32. የመኖ ምርቶችንና ግብዓቶችን ለሌላ አካል ስለማስተላለፍ

ማንኛውም ሥራውን በራሱ ፈቃድ ያቋረጠ፣ ዕገዳ ወይም ስረዛ የተጣለበት ድርጅት በእጁ ጥቅም ላይ መዋል የሚችል መኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገርወይም ግብዓት በባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትላላቸው ሌሎች ድርጅቶች ከተሟላ መረጃዎች ጋር የባለሥልጣኑ የምዝገባና ፈቃድ ባለሙያዎች በተገኙበት በሥርዓት ማስተላለፍ ይገባዋል፡፡

## 33. መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችን ስለመያዝ

1. ባለስልጣኑ መኖ ወይም በመኖ ግብዓቶች ጥራትናደህንነት ላይ ጉድለትመኖኑንጥርጣሬሲኖረውወይምበእንስሳትና በህብረተሰቡ ጤናላይአደጋሊያደርስይችላልብሎ ካመነበት መኖ ወይም የመኖ ግብዓቶችን ጥራትናደህንነትእስኪረጋገጥድረስ ምርቱ ተይዞና ለብቻውተገልሎ እንዲቆይሊያደርግይችላል፣
2. በዚህአንቀፅንዑስ አንቀፅ1 መሠረት ተገልሎ እንዲቆይ የተደረገ መኖ ወይም የመኖግብዓትአስፈላጊው ፍተሻ ተደርጎ በጥቅም ላይ የማይውል መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ምርቱ ሊወገድ ወይም ወደ መጣበት ሀገር ሊመለስ ይችላል፤
3. በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 23 እስከ 29 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በመተላለፍ የሚደረግየመኖ ሕገ-ወጥ ንግድና ዝውውር በተመለከተ ከኅብረተሰቡ ጥቆማ ሲደርሰው ባለሥልጣኑ ወይም ቅርንጫፍ መ/ቤቶቹ የምርቱን ጤናማነትና ደህንነት እንዲሁም ሕጋዊ አሠራሮችን ስለመከተላቸው ለማረጋገጥ ምርቱን መያዝ ይችላል፡፡

## 34. የመኖ ምርት ከገበያ ስለመሰብሰብ (Feed Products Recall)

1. ማንኛውም የመኖ ንግድ ድርጅት ያሰራጨው ምርት ጥራትና ደህንነት ጥርጣሬ

ውስጥየሚያስገባ ጠቋሚ መረጃዎች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ማንኛውም ዓይነት ሽያጭ እንዳይደረግ የማስቆምና ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፣

2. ማንኛውም የመኖ ንግድ ድርጅት ያስመጣው ወይም ያሰራጨው የመኖ ምርት ጥራትናደህንነትጉድለት ካለውና ለእንስሳትና ለህብረተሰቡ ጤና ጎጂ መሆኑ ሲረጋገጥ በራሱ አሠራርናወጪ ከገበያየመሰብሰብ ግዴታ አለበት፣
3. በደህንነትና የጥራት ጉድለት ምክንያት ከገበያ የተሰበሰበዉ መኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ወይም ግብዓት በላቦራቶሪ ፍተሻ ሲረጋገጥ በአንቀጽ 36 መሠረት እንዲወገድ መደረግ አለበት፣
4. የመኖ ምርት ወይም የመኖ ግብዓት ብልሽት ምክንያቱ ተጣርቶ ችግሩ እንዲከሰት ያደረገውድርጅት አግባብ ባላቸው ሕጎች አስተዳዳራዊ ወይም ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ይደረጋል፡፡

## 35. ጥቅም ላይ የማይውሉ የመኖ ምርቶችንና ንጥረ ነገሮችንወይምግብዓቶችን ስለማስወገድ

1. ማንኛውም መኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገሮችወይም ግብዓቶች ንግድ ድርጅት በተለያዩ ምክንያቶች ጥቅም ላይ የማይውሉ የመኖምርቶችንናንጥረ-ነገሮችንወይም ግብዓቶችን ለይቶ የመያዝና ዝርዝራቸውን ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ጥቅም ላይ የማይውሉ የመኖ ምርቶችና የመኖንጥረ-ነገሮችወይም ግብዓቶች በባለሥልጣኑ ውሳኔና የአሠራር መመሪያ መሠረት እንዲወገዱመደረግ አለበት፣
3. ማንኛዉም ጥቅም ላይ የማይውል መኖ እና የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይም ግብዓቶች የሚወገዱት አካባቢን በማይበክል ሁኔታ ለዚህ ተግባር በባለሥልጣኑ በሚቋቋም አስወጋጅ ኮሚቴ የሚከናወን ይሆናል፣
4. ማንኛውም ጥቅም ላይ የማይውል መኖ እና የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይም ግብዓቶች በሚወገዱበት ጊዜየማስወገጃ ሙሉ ወጪውን የሚሸፍነው የንግድ ድርጅቱ ይሆናል፣
5. በዚህ አንቀጽ መሠረት ለተወገደ መኖ ወይም የመኖ ንጥረ-ነገሮችወይምግብዓቶች ባለሥልጣኑ ሕጋዊ ማስረጃ ለመኖ ንግድ ድርጅቱ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 36. በባለስልጣኑበሚወሰዱ አስተዳዳራዊ እርምጃዎች ላይ የቅሬታ አቀራረብ ሂደት

1. በሚወሰዱ አስተዳዳራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ የሚቀርበው በባለስልጣኑ የአስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ መሠረት ይሆናል፣
2. ማንኛዉም የመኖ ንግድ ድርጅት ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ዕድሳት ፣ ዕገዳናስረዛ ወይም ሌሎች ባለሥልጣኑ በሚወስዳቸዉ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ የተሰማው አካል አቤቱታውን በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ በባለስልጣኑ ለተቋቋመዉቅሬታ

ሰሚ አካልማቅረብ ይችላል፣

3. የባለሥልጣኑ ቅሬታ ሰሚ አካልም የቀረበለትን ቅሬታ በማጣራት በ30 ቀናት ውስጥ አግባብነትያለው ምላሽ ለአመልካቹ መስጠት ይኖርበታል፣
4. ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ባያገኝ ወይም የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኖሳያገኘው ቢቀር ቅሬታውን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት መውሰድ ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 37. የመኖ ሚዛን ስለ ማያዝ

1. ማንኛዉም የመኖ ንግድ ድርጅት ለሚያመርታቸው፣ ለሚያስመጣቸውና ለሚያከፋፍላቸው የመኖ ዓይነቶችንና ጥሬ ዕቃዎችንወይም ግብዓቶችን ምንጭና መነሻ ዝርዝር መረጃ (for traceability) ለይቶ መያዝ አለበት፣
2. ማንኛዉም መኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገርወይምግብዓት ንግድ ድርጅት ስለ አመረተው ወይም ስለአስመጣው፣ስለአከፋፈለው፣ስለላከዉ፣ ስለተበላሸው፣ የመጠቀሚያ ጊዜዉ ስለአለፈበት፣ ስለተወገደ እና ሌሎች ከመኖ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች በአግባቡ የመያዝና በባለስልጣኑ ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት፣
3. የመኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገሮችወይምግብዓቶች ንግድ ድርጅት ዝርዝር ደረሰኞች፣ የክምችትመቆጣጠሪያ ስቶክካርዶችንና ቢን ካርዶችን እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችን በአግባቡ መያዝ ይኖርበታል፣
4. ማንኛውምየመኖ ንግድ ድርጅት የመኖ ምርቶችን ወይም የመኖ ግብዓቶችን የገዛበትና የሸጠላቸውን ድርጅቶች ስምና ሙሉ አድራሻ በዝርዝር መያዝ አለበት፣
2. ማንኛዉንም የመኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገሮችወይምግብዓቶች ንግድ ድርጅት ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች ወቅታዊነት ቢያንስ ለ3 ዓመታት በአግባቡ የመያዝና ለባለሥልጣኑና ሌሎች ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችም ጭምር ግልፅ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

### 38. የመኖ ምርት ወይምግብዓት የንግድ ማስታወቂያ አሠራር

ማንኛውም የእንስሳት መኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገሮችወይምግብዓቶች የንግድ ማስታወቂያ ሂደትና ይዘት የሚከተሉትን ዋና ዋና መሠረት ሐሳቦችን የተከተለ መሆን ይገበዋል፡፡

1. ማንኛውም የእንስሳት መኖ የንግድ ማስታወቂያ አቅራቢ ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ ማስታወቂያማውጣትና ማስነገር የለበትም፣

2. የእንስሳት መኖ የንግድ ማስታወቂያ የመንግሥትን የማስታወቂያ ሥርዓትና ሥነምግባር አክብሮ መዘጋጀትና መቅረብ አለበት፣
3. ለማስታወቂያ የተዘጋጀው የመኖ ምርት ለየትኛው የእንስሳት ዓይነት፣ የዕድሜ ክልልና የምርት ክፍሎች መጠቀም እንደሚገባ በግልጽ መጠቀስ አለበት፡፡ ለምሳሌ፡- ለታላቢ የዳልጋ ከብት፣ ለአጥቢ እናቲትበግ ወይም ፍየል፣ ለዕንቁላል ጣይ ዶሮ፣ ለአሳማ፣ ለጥጃ፣ ለጫጩት፣ ለዳልጋ ከብትማድለቢያ፣ለበግ/ፍየል ማድለቢያወ.ዘ.ተ በሚል ሁኔታ በግልጽ ተዘርዝሮ መገለጽ አለበት፤
4. የመኖ ንግድ ማስታወቂያ ከመውጣቱና አየር ላይ ከመዋሉ በፊት የመኖ ምርቱ ከምን ዓይነት ግብዓቶች እንደተቀነባበረ፣ የቅንብር ሂደትና የንጥረ ነገሮችን ዝርዝር መግለጫ የያዘየማስታወቂያው ረቂቅ ጽሑፍ በማስታወቂያው አቅራቢ ድርጅት በኩል ለባለስልጣኑ ቀርቦ መፈቀድአለበት፣
5. ማስታወቂያው የሌላውን መኖ አምራች፤ አስመጪ፤ አከፋፋይ ወይም የሌላውን ተወዳዳሪ ድርጅትምርት፤ ጥራት ደረጃ እና ደህንነት እንዲሁም የንግድ ምልክት ማጥላላት፣ አሳንሶ ማቅረብ ከማስታወቂያ ሥነ-ምግባር ውጭ እንዳይሆን ባለሥልጣኑ ለዚህ ጉዳይ በሚመድበው ክፍልና ባለሙያ አማካኝነት ታይቶ መፈቀድና ማለፍ ይገባዋል፣
6. በምርት ገላጭ ጽሁፍ ላይ ከተመለከተው የእንስሳት ዓይነት፣ የዕድሜና የምርት ክፍል ውጪመመገብ የተከለከለ ስለመሆኑ መጠቀስና መገለጽአለበት፣
7. ማስታወቂያው ሲወጣም ሆነ ሲነገር ከሌላ የእንስሳት መኖ፣ የእንስሳት መድኃኒት፣ ለሰው ምግብሊውሉ ከሚችሉ ማስታቂያዎች ጋር የሚጣረስ መሆን የለበትም፣
8. በመኖ ንግድ ማስታወቂያ ላይ የመኖ አጠቃቀምን በተመለከተ በከፍተኛ ጥንቃቄ እና በባለሙያመታገዝ እንዳለበት አበክሮ መገለጽ አለበት፣
9. በማስታወቂያው ላይ ለእንስሳት የሚቀርብ መኖ ንጽህናው በተጠበቀ ዕቃና ለእንስሳት ክብካቤ ኃላፊነት በተሰጠው ሰው እንዲሁም በእንስሳት አመጋገብ ባህሪ ላይ ተመርኩዞ መሰጠት እንዳለበትመገለጽ ይገባዋል፣
10. የመኖ ንግድ ማስታወቂያ የእንስሳትን ጤንነትንና ደህንነት መርሆዎችን በማያዛባና በማይጎዳመልኩ መዘጋጀትና መውጣት አለበት፣
11. የመኖ ንግድ ማስታወቂያ የሀገሪቱን ህዝብ ባህል፣ እምነትና ተለምዶ በማይጻረር መልኩ በጥንቃቄ መዘጋጀትና መቅረብ አለበት፣
12. በማስታወቂያ የሚነገረው መኖ የእንስሳት በሽታን ያድናል ወይም ይፈውሳል፣ ጤና ያሻሽላልተብሎ መነገር የለበትም፣

13. እንደ መኖዉ ዓይነት የእንስሳት ምርታማነትን የሚደግፍ፣ የሚረዳ፣ ጉልበት የሚሰጥ ለእንስሳት አካላት ዕድገት ጠቃሚ ነው ተብሎ ሊነገር ይችላል፤
14. በቀጥታ ለእንስሳት የማይሰጥ የመኖ ተጨማሪ ንጥር ነገር ከምግብና ከውሃ ጋር በማመጣጠንየሚሰጥ መኖ በባለሙያና በፋብሪካው ገላጭ ጽሑፍ በሚያዘው መሠረት ብቻ እንደሚሰጥናጠቃሚነቱም መኖን ለማዋሃድ፣ ለመፍጨት እንዲሁም የተሻለ ምርት ለመስጠት የሚያግዝእንዲሁም ለተጠቃሚው የጎንዮሽ ጉዳት የማያስከትል ስለመሆኑ በመግለጽ መውጣት ይችላል፤
15. በኤሌክትሮኒክስ ግብይት (e-marketing) የሚካሄድ ግንኙነት የድርጅቱን የንግድ ስም፣ ሙሉአድራሻ፣ የምርት መለያ ቁጥር (butch number)፣ ለየትኛው የእንስሳት ምርትና ዕድሜ ክፍል መዋል እንዳለበት፣ ምርቱ የታሸገበት ቁስ፣ የተመረተበት ቀንና ዓ.ም፣ በመጋዘን የሚቆይበትጊዜ ወይም መጠቀሚያ ጊዜ (storage life)፣ ምርቱ ከታዘዘ በኃላ የሚቀርብበት ጊዜ፣የተመረተበት ሀገር በዝርዝር መጠቀስ አለበት፡፡

## 39. የ መኖ መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለ ማድረግ

1. ባለሥልጣኑ የወሰደውን ማንኛውም አስተዳዳራዊ እርምጃ በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የቅሬታ አቀራረብ ጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅወይም ቅሬታ ሰሚ አካሉ ጉዳዩን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ መረጃዎቹን ለህብረተሰቡ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፣
2. ባለሥልጣኑ በማንኛውም የመኖ ንግድ ድርጅ ያገኛቸው የአሠራር ግድፈቶች፣ የተረጋገጠ ተጨባጭ ጥቆማዎችና መረጃው ለሕብረተሰቡ ባለመነገሩ በእንስሳትና በህብረተሰቡ ጤናላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ሲታመን መረጃዎቹን አመቺ ሆኖ ባገኘው የመገናኛዘዴ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፣
3. ማንኛውም የመኖ ንግድ ድርጅት የድርጅቱን ስምና አድራሻ የሚገልፅ፣ ሊነበብ በሚችል ጉልህፊደል ቢያንስ ድርጅቱ በሚገኝበት የአካባቢ ቋንቋ ወይም በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ፅፎ ድርጅቱ በሚገኝበትቦታ ላይየድርጅቱን ማንነት ሊያመላክት በሚችል መልኩ ማኖር አለበት፣
4. ባለሥልጣኑ ማንኛውም ጠቃሚ የመኖ መረጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችናባለሙያዎች ይፋ ሊያደርግ ይችላል፣
5. በባለሥልጣኑ ምስጢር ተብለው ከተያዙ መረጃዎች በስተቀር ስለ ማንኛውምመኖ ወይም የመኖ ንጥረ ነገርወይም ግብዓትማንኛዉም ሰዉ የሚፈልገውን መረጃ ማግኘት ይችላል፡፡

## 40. የአገልግሎት ክፍያ

ማንኛዉምመኖ ወይም የመኖ ግብዓት ንግድ ድርጅት በባለስልጣኑ ለሚሰጠው አገልግሎት አግባብ ባለው አካል በሚወስነው የክፍያ ተመን መሠረትክፍያውን በቅድሚያ መፈጸም

ይኖርበታል፡፡ የአገልግሎት ክፍያው መጠን ዝርዝር ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ ደንብ የሚገለጽ ይሆናል፡፡

## 41. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ ሰርኩላር፣ ደብዳቤ፣ የአሠራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 42. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ **ከህዳር** 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ጠርዙ ዳያ ደጋጋ (ዶ/ር)**

**የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥርባለስልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**

## 43. ዕዝሎች

የእንስሳትመድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለልጣን

Veterinary Drug and Animal Feed Administration andControl Authority

**ዕዝል 01**

## የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መጠየቂያ ቅጽ

1. የአመልካቹ ሙሉ ስም __________________________-
____________________________________________
2. የአመልካች ድርጅት ስም __________________________ የንግድ ስም
__________________________________
3. አመልካቹ በድርጅቱ ውስጥ ያለው
ኃላፊነት_______________________________________________________
4. የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ
ስም__________________________________________________________________

አድራሻ ፡- ክልል __________________ ክ/ከተማ (ዞን) ወረዳ __________ ከተማ_________________________
ስልክ ቁ.__________ ሞባይል _________________ ኢ.ሜይል____________________________________________

5. የመኖ ንግድ ድርጅቱ አድራሻ

ክልል_____________________ (ዞን) ክ/ከተማ____________ወረዳ___________________ከተማ____________________
ስልክ ቁ_______________ሞባይል________________________ኢ.ሜል________________________________
የቦታው ልዩ መጠሪያ_____________________________________________________________________

6. የድርጅቱ ዓይነት

የመኖ አስመጪና አከፋፋይ ☐ የመኖ አምራችና አከፋፋይ ☐ የመኖ አምራችና ላኪ ☐
የመኖ አከፋፋይ ☐

7. የድርጅቱ የመኖ ቴክኒክ ሠራተኛ ወይም ባለሙያ

7.1 ሙሉ ስም __________________________________
7.2 የትምህርት ደረጃ ____________________________
7.3 የባለሙያው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቅጅ (አብሮ ይያያዝ)
7.4 የሠራተኛው/ባለሙያው የውል ስምምነትና የትምህርት ማስረጃ ቅጅ (አብሮ ይያያዝ)

8. እኔ __________________________ የተባልኩኝ የመኖ አምራችና አከፋፋይ፣ አስመጪ አከፋፋይ፣ አምራችና ላኪና ድርጅት የምዝገባና የሥራ ፈቃድ መስጫ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟላሁ ስለሆነ ድርጅቱ ታይቶ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ፡፡

ፊርማ _________________________________

ቀን _____________________________

9. <u>ለቢሮ ሥራ ብቻ የሚያገለግል</u>

ማመልከቻውን የተቀበለው ባለሙያ ስም ________________________________

ማመለልከቻውን የተቀበለበት ቀን ____________________

መልስ የሚሰጥበት ቀን (ቀጠሮ) _______________________

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስጣን

Veterinary Drug and Animal Feed Administration andControl Authority

**ዕዝል 02**

## የመኖ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለመስጠት

## በብቃት ፍተሻ ባለሙያዎች የሚሞላ ቅፅ

ድርጅቱ ስም ______________________የምርት ዓይነት __________________

ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ፡ ክልል ___________ ዞን/ክፍለ ከተማ ________ወረዳ _________ ከተማ_____________

ቀበሌ _______________ የቦታው ልዩ መጠሪያ _____________ ስልክ ቁጥር _________ ሞባይል ___________________

የድርጅቱ ባለቤት ወይም ተወካይ ____________________________

የባለሙያዎች ማጠቃለያ አስተያየት ______________________________________________________________

| ተቁ | የመገምገሚያ መስፈርት | የመመዘኛ ነጥብ | የተሰጠ ነጥብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ድርጅቱ የተቋቋመበት ቦታ ለመኖ ብክለት ያለው ተጋላጭነት | 7 | |
| 2 | የመኖ ማምራቻ ሂደትእንደአመራረት ባህሪዩ የተሟላ የቴክኒክ ሂደት ያለው ስለመሆኑ | 10 | |
| 3 | የመጋዘን ከፍታ ከሚከማቸው መኖ መጠንና የአየር ሁኔታ ጋር የሚኖረው ተስማሚነት | 5 | |
| 4 | ድርጅቱ ከሚያከማቸው የመኖ መጠን አንፃር የክፍሎቹ ስፋት ሁኔታ | 5 | |
| 5 | ለተበላሹ፣የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው መኖ ማቆያ የተለየ ክፍል፣ | 5 | |
| 6 | የማከማቻ ክፍሉ ጣሪያ የተሰራበት ማተሪያል ሙቀትና ከቀጥተኛ የፀሀይ ብርሃን የመከላከል አቅሙ | 5 | |
| 7 | የማከማቻ መጋዘኑ በር፣ መስኮት እና የአየር ማስገቢያ ነፍሳትና ተባይ እንዲሁም መኖውን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች የመከላከል አቅሙ | 10 | |
| 8 | በማከማቻ መጋዘኑ ውስጥ ያለው የብርሃንና የአየር ዝውውር ሁኔታ በቂ ስለመሆኑ | 7 | |
| 9 | ለፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ሁኔታ ያለው አስፈላጊ ግንባታና ቁሳቁስ | 8 | |
| 10 | መኖውን ለማቆየት የሚያስችል በቂ መደርደሪያ ወይም ፓሌት መኖሩንና የማቴሪያሉ ዓይነት | 6 | |
| 11 | የድንገተኛ እሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ ስለመኖሩ | 5 | |
| 12 | የመኖ መሸጫና ስርጭት መረጃ መያዣ ስርዓት ስለመኖሩ | 5 | |
| 13 | ድርጅቱን በቴክኒክ ኃላፊነት የሚመራ የመኖ ሽያጭ ሠራተኛ /ባለሙያ የትምህርት ዝግጅት ሁኔታ | 8 | |
| 14 | የሠራተኞች የሥራ ጤናማነትና ደህንነት መጠበቂያ ክፍሎችና ማቴሪያሎች መኖራቸው | 6 | |
| 15 | የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መሳሪያ መኖሩን | 4 | |
| 16 | መፀዳጃና የእጅ መታጠቢያ ክፍል መኖሩ | 4 | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | 100 | |

______________________________________________________________________________

| የባለሙያዎች ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| 1.____________________ | ______ | |
| 2.____________________ | _______ | ________________ |
| 3.____________________ | ______ | |

የኃላፊው አስተያየት __________________________________________________

ስም ___________________ ፊርማ ____________________ቀን _________ ሰዓት _______

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለልጣን
Veterinary Drug and Animal Feed Administration andControl Authority

**ዕዝል 03**

## በተስማሚነት ፍተሻ ወቅት የተገኙ ክፍተቶችን ለማሟላት ከድርጅቱ ጋር የሚገባ መተማመኛ ሰነድ

የድርጅቱ ስም ______________________________ ምርት ዓይነት ____________________

የድርጅቱ አድራሻ ክልል ______________ ዞን/ክ/ከተማ ________________ወረዳ ___________ ከተማ ______________

ስልክ _______________ ፋክስ _________________ E-mail: ____________________

የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ ____________________________________________

| ተ.ቁ | በድርጅቱ ውስጥ የተገኙ ክፍተቶች | በድርጅቱ መወሰድ ያለባቸው የማስተካከያ እርምጃዎች | የጊዜ ወሰን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | |
| 2 | | | | |
| 3 | | | | |
| 4 | | | | |
| 5 | | | | |
| 6 | | | | |
| 7 | | | | |

| | |
|---|---|
| የፈታሽ ባለሙያዎች ስም ፊርማ | |
| 1. | የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ |
| 2. | ስም |
| 3. | ፊርማ |
| ቀን | ቀን |
| | |

Veterinary Drug and Animal Feed Administration andControl Authority

ዕዝል 04

**የመኖ አምራች፣ አስመጪ፣ ጅምላ አከፋፋይ፣ ላኪ ንግድ ደርጅት የብቃት ማረጋጋጫ ምስክር ወረቀት**
Certificate of Competence for Feed Processors, Importers, Exporters, Wholesalers Organizations

ቁጥር ________________

ቀን _________________

የድርጅቱ ስም ___________________ የንግድ ስራ ዓይነት____________________________
Name of business organization Buisness type
የሚይዘው የምርት ዓይነት____________________________________________________________
Product Type
የድርጅቱ አድራሻ
Address of the organization
ክልል_________________ዞን/ክ/ከተማ _______________ወረዳ ___________ከተማ _____________
Region Sub city/Zone Woreda City

ቀበሌ _____________ የቤ/ቁጥር__________ስ/ቁጥር __________________ፋክስ______________Kebele
Kebele House no Telephone Fax

የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ ስም ___________________________________
Owners Full Name
ድርጅቱ ባለስልጣኑ ያወጣውን መስፈርቶች ማሟላቱ ስለተረጋገጠ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥተር 728/2004 አንቀጥ 19 መሠረት ለ __________________________________________ የሥራ ፈቃድ መስጫ መደብ ቁጥር _________________ ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

This Certificate of Competence is issued for Business type _____________________________ work permit # ___________, upon fulfillment of requirements set by the Authority in accordance with Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Proclamation No. 728/2011 Article 19.

_________________________ ____________________
የኃላፊ ፊርማ የተሰጠበት ቀን
Signature of Authorized Person Date of Issue

| | | |
|---|---|---|
| ታድሷል 200___________ | ታድሷል 200 _______ | ታድሷል 200_______ |
| Renewed 200________ | Renewed 200 _____ | Renewed 200 _______ |
| የደረሰኝ ቁጥር _________ | የደረሰኝ ቁጥር _______ | የደረሰኝ ቁጥር ________ |
| R/no________________ | R/no _____________ | R/no ____________ |
| ፊርማ _____________ | ፊርማ _____________ | ፊርማ __________ |
| Sig _______________ | Sig _____________ | Sig ____________ |

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለልጣን

Veterinary Drug and Animal Feed Administration andControl Authority

**ዕዝል 05**

### የመኖ ናሙና መውሰጃ ማሳወቂያ ቅጽ

እኛ ስማችን ከታች የተገለፀው የባለስልጣኑ ባለሙያዎችና ኢንስፔክተሮች የሆንን በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ (ሐ) ና (መ) መሠረት የሚከተለውን የመኖ ናሙና ለምርመራ ዓላማ ከድርጅቱ የወሰድን መሆናችንን እናረጋግጣለን፡፡

1. የናሙናው ባለቤት ድርጅት ስም ______________________________
2. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቁጥር ______________________________
3. አድራሻ ______________________________
4. የናሙናው መጠሪያ ስም እና አይነት ______________________________
5. መጠን ______________________________
6. የምርት መለያ ቁጥር (batch No.) ______________________________
7. የተመረተበት ቀን ______________________________
8. የመጠቀሚያ ጊዜው የሚያበቃበት ቀን ______________________________
9. የአምራቹ ድርጅት ስም ______________________________
10. ናሙናው የተወሰደበት ቦታ ______________________________
11. ናሙናው የተወሰደበት ምክንያት ______________________________

ናሙናውን የወሰዱ ባለሙያዎች ወይም ኢንስፔክተሮች ሙሉ ስም

1. ______________ ፊርማ ______
2. ______________ ፊርማ ______
3. ______________ ፊርማ ______

የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ

ስም ______________

ፊርማ ____________

ቀን ___________

ናሙናው የተወሰደበት ቀን _______ ሰዓት ______

የባለሙያዎች ወይም ኢንስፔክተሮች ኃላፊ አስተያየት

______________________________________________________________

______________________________________________________________

የኃላፊው ሙሉ ስም________________________

ፊርማ ________________________

ቀን ________________________

የእንስሳት መድኃኒ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን

Veterinary Drug and Animal Feed Adminstration & Control Authority

ዕዝል 06

## የመኖ ናሙና ወደ ላቦራቶሪ መላኪያ ቅፅ

ለ ______________________________________________________________

በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 1-2 መሠረት የሚከተለውን የመኖ ናሙና ለላቦራቶሪ ምርመራ ዓላማ የተላከ መሆኑን እየገለፅን ናሙናው ተመርምሮ ውጤቱ እንዲገለፅልን ትብብር እንጠይቃለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1 | የናሙናው መጠሪያ ስም | |
| 2 | ለናሙናው የተሰጠ መለያ ቁጥር | |
| 3 | የናሙናው መጠን | |
| 4 | የምርት መለያ ቁጥር (Batch No) | |
| 5 | የመኖው ናሙና ተመረተበት ቀን | |
| 6 | መጠቀሚያው ጊዜ የሚያበቃበት ቀን | |
| 7 | የናሙናው ምርመራ ያስፈለገበት ምክንያት | |
| | | |
| | | |
| 8 | የምርመራው ዓይነት | ማይክሮባዮሎጊካል፣ ፊዚኮኬሚካል፣ ቶክሲሲቲ፣ ኑትሪሺናል ይዘት |
| | | |
| | | |
| 9 | ናሙናውን የላከው ኃላፊ | |
| | ሙሉ ስም | |
| | ፊርማ | |
| | ቀን | |

የእንስሳት መድኃኒትና ተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን

Veterinary Drug and Animal Feed Adminstration & Control Authority

**ዕዝል 07**

Telephone: 251- 115 50 86 70
Fax: +2511___________
P.O.Box : 31303
E-mail: __________________
Website: http://www. __________
Addiss Ababa, Ethiopia

Ref. No
_______/_______/________

Date:
_______/____/______

## Animal Feed Sanitary/Phytosanitary Certificate (Template)

This is to certify that __________________________ Ltd, Address______________________ Ethiopia is registered under certificate of competence No ___________ in accordance with the Veterinary Drug and Animal Feed Admnistration and Control Authority, proclamation no. 728/20011 of The House of Represenatatives of the FDRE, as Animal Feed ______________________. The Feedd is inspected to ascertain compliance with the prescribed standard.

Permission is hereby granted to it for export of _________________ Metric Tons (Kg) of ___________________to _____________________ as here under shown.

Name of Feed, ____________________________________________, Invoice Number______________ Batch no __________________ , Total Quantity (MT) or kg_______________ Values ______________ ($USD), remarks ____________________________________________________________________.

Please note that this Sanitary Certificate is limited to this consignment only, and is Valid from Date ______/_____/_____ to Date____/____/______.

Sig __________________________
Responsible Cretifying Directorate

Stamp